ሠመራ ዩኒቨርሲቲ

አመታዊ መፅሔት

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ በ2016 ትምህርት ዘመን የተከናወኑ አበይት ተግባራትን ያጠቃለለ አመታዊ መፅሔት

በህዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈፃሚ እና ፕሬዚደንት ጽ/ቤት ትብብር የተዘጋጀ



የሠመራ ዩኒቨርሲቲ አመታዊ መፅሔት

የአዘጋጆች መልእክት

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የተሰጠውን ተግባር ተኮር የመማር ማስተማር፣ ችግር ፈች ምርምር ስራዎችን የመስራት ተልእኮ ለማስፈፀም እስተራቴጅክ እቅድ አዘጋጅቶ በቁርጠኝነት ወደ ተግባር እየገባ ሲሆን ከዚህ አኳያ ለተልእኮው መሳካት ይረዳው ዘንድ እንደ ትኩረት አቅጣጫ ካስቀመጣቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል፤ወደ አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ መሸጋገር ፣ የልህቀት መስኮች ትግበራ እና የትምህርት ጥራት ትግበራ እንዲሁም ስራዎችን በቴክኖሎጂ መደገፍ ናቸው።

ከላይ የተቀመጡትን ጉዳዮች ለመተግበር እና በአደረጃጀት ለማጠናከር በሰው ኃይልና በግብአት፣ የተማሪዎች ቅበላን በማሳደግ የተግባር ትምህርት መስጫ ተቋማትን /ላብራቶሪዎችና ሰርቶ ማሳያና ምርምር ማዕከላትን/ ማደራጀትና ማጠናከር መሰራት አለባቸው።

ይህ አመታዊ መጽሄት በ2016 ትምህርት ዘመን በሠመራ ዩኒቨርሲቲ አመቱን በሙሉ የተከናወኑ ስራዎችን እና አፈጻፀማቸውን መሰረት ያደረገ እንዲሁም ቃለ መጠይቆችንም ያካተተ መሆኑን እያመላከትን መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ ምኞታችን ነው ።



ማውጫ

የይዘት ዝርዝር

1. የአዘጋጁ መልእክት
2. ሀገር አቀፍ መድረኮች
3. ተቋማዊ መድረኮች
4. ጉድኝቶች
5. ድጋፍ
6. ማህበረሰብ አገልግሎት
7. ምርምር ሥራዎች
8. አቅም ግንባታ ስልጠና
9. ጉብኝት
10. ክብረ በአላት
11. እውቅና
12. ስፖርት
13. ስለ ዩኒቨርሲቲው የተሰጡ ምስክርነት
14. አርአያ ሰብእ

Scan and Join

For More Updates, be a member of SU's official social networking pages.

ፌስቡክ
https://www.facebook.com/susamara2008/
ቴሌግራም
https://t.me/SamaraUniversityEthiopia
ዩትዩብ
https://youtube.com/channel/UCvDWGawVYKQa_FJY8supkBA?sub_confirmation=1
ዌብሳይት
Www.su.edu.et
ትዊተር
https://twitter.com/SamaraunivEthio?t=QlDpWx8vlY_udWdGAztwvg&s=09
ሊንደን
https://www.linkedin.com/company/samara-university-ethiopia/
ቲክቶክ
https://www.tiktok.com/@samara.university?_t=8ipUGAsrMwg&_r=1

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት www.su.edu.et ታህሳስ/2017/24

ሀገር አቀፍ መድረኮች

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሀገር ግንባታ!

ለሀገራዊ ማንነትና እሴት ግንባታ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚና ለሀገር ግንባታ!



"ለሀገራዊ ማንነትና እሴት ግንባታ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚና" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሀገራዊ የምክክር መድረክ በአራት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሠመራ፣ ወልድያ፣ ወሎ እና ራያ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ በመሆን አካሂደዋል::

በዚህ መድረክ ላይ 'ዳሎል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፎረም' ተመስርቷል።





ፎረሙ ሁሉንም ዩኒቨርሲቲዎች በማቀፍ እውቀትንና ሀብትን በማስተባበር ለሀገር ግንባታ ግብአት የሚሆኑ የምክክር መድረኮችን: ጥናትና ምርምሮችን እንዲሁም ሀገራዊ ዕሴቶችን በማስተማር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሀገር ግንባታ የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ የሚያስተባብር ነው::

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት መሀመድ ኡስማን (ዶ/ር) የፎረሙ ሰብሳቢ ሆነው የተመረጡ ሲሆን የአራቱን ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዚዳንቶች የመሰራች ኮሚቴ አባል እና ከአራቱም ዩኒቨርሲቲዎች የተመረጡ አራት ምሁራንን ደግሞ የቴክኒክ ኮሚቴ አድርጎ መርጧል።

ሀገር አቀፍ መድረኮች

ቀይ ባህር

ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ቀጠና ያላት ፍላጎት - ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት

ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ቀጣና ያላት ስትራቴጂካዊ ፍላጎት ላይ ያተኮረ ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከአዲስ አበባ፣ ከመቀሌ፣ ከድሬዳዋ እና ከጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር አዘጋጅተዋል።

አውደ ጥናቱ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ቀጠና ላይ ያላትን ስትራቴጂካዊ ፍላጎት በሚመለከት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በምርምር የታገዙ ተጨባጭ ምልከታዎች የቀረቡበት ነው።

- ሰመራ ዩኒቨርሲቲ
- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
- መቀሌ ዩኒቨርሲቲ
- ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
- ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ



ሰመራ ዩኒቨርሲቲም ለቀይ ባህር ቀጣና ቅርብ ከመሆኑ አኳያ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማረጋገጥና የህዝብ ለህዝብ ትስስርን ለማጠናከር የምርምር አውዶችን ለይቶ እንደሚሰራ ተጠቁሟል።



"አድዋን ለጠንካራ ሀገረ-መንግሰት ግንባታ" ሀገራዊ የምክክር መድረክ



በምክክር መድረኩ የክብር እንግዶች የሠላም ሚኒስቴር ሚኒስተር ዲኤታ ዶ/ር ከይረዲን ተዘራ እንዲሁም የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት፣ የአፋር ክልል አመራሮች፣ የዩኒቨርሲቲዉ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች፣ የሃይማኖች አባቶች ፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ተወካዮች ፣ የፌደራል ፖሊስ አባላት እና ተማሪዎች ተገኝተዋል።

መድረኩ አባቶቻችን በአድዋ ያስገኙትን ድል ለጠንካራ ሀገረ-መንግስት ግንባታ፣ ለሰላምና ለልማት እንጠቀምበት በሚል ሀሳብ የተዘጋጀ ነው::

አድዋን ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ሀገረ-መንግስት ግንባታ ብሎም ሀገራዊ እሴቶቻችንን ለማጎልበት እንደ ተምሳሌት ወስዶ ጥቅሞቻችን ማስጠበቂያ መሆን እንዳለበት ተገልጧል።





“ዘመኑን የዋጀ አርበኝነት ለሀገራዊ አንድነት ” ሀገር አቀፍ የምክክር መድረክ

በዩኒቨርሲቲው “ዘመኑን የዋጀ አርበኝነት ለሀገራዊ አንድነት ” በሚል ርዕስ ሀገር አቀፍ የምክክር መድረክ ተካሂዷል::

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ከኢፌዲሪ ሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር “ዘመኑን የዋጀ አርበኝነት ለሀገራዊ አንድነት” በሚልርዕስ ያዘጋጁት የምክክር መድረክ አካሂደዋል::







ሀገር አቀፍ መድረኮች "The Economic Cost of Conflict and Options for Recovery"

የመጀመሪያው ዓመታዊ ኮንፈረንስ"The Economic Cost of Conflict and Options for Recovery"



የግጭት ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ፣የተቋማት ሚና እና ፖሊሲ፣የማገገሚያ ስትራቴጂዎች ላይ ሶስት የውይይት መነሻ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው በተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል።

በተያያዘ ዜና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር፣ የአፋር ክልል ፕላንና ልማት ቢሮ፣ ሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና የአፋር መልሶ ማቋቋምና መልሶ ግንባታ ፈንድ ጽ/ቤት መካከል የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተፈርሟል።

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የኢኮኖሚ እድገት ላይ ያተኮረ የመጀመሪያው አመታዊ ኮንፈረንስ "The Economic Cost of Conflict and Options for Recovery" በሚል መሪ ሀሳብ ግንቦት 17 ቀን 2016ዓ.ም በሠመራ ከተማ ተካሂዷል።

ኮንፈረንሱ Friedrich Ebert Stiftung, የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር እና ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በጋራ ያዘጋጁት ሲሆን የኮንፈረንሱ አላማ ግጭቶች የሚያደርሱትን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ለመቅረፍ:ለማገገምና ለዘላቂ ልማት አዋጭ መንገዶችን ለመቃኘት ነው ተብሏል።





ሀገር አቀፍ መድረኮች

የአዋሽ ቤዚን የንዑስ ተፋሰሶች ምስረታ

የአዋሽ ቤዚን የንዑስ ተፋሰሶች የባለድርሻ አካላት ፕላትፎርም ምስረታ መድረክ

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከኢፌዲሪ የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ያዘጋጁት የአዋሽ ቤዚን ንዑስ ተፋሰሶች ባለ ድርሻ አካላት ፕላትፎርም ምስረታ መድረክ በሰመራ ከተማ ተካዷል።



የመድረኩ ዓላማ የኢትዮጵያ ወሳኝ የውሃ ሀብት የሆነውን የአዋሽ ተፋሰስ ሁሉን አቀፍ የባለድርሻ አካላት መድረክ ለመመስረት መሆኑ ተገልጿል።

ፕላትፎርሙ የአዋሽ ተፋሰሶችን ዘላቂ ጥቅምና ጥበቃ እንዲሁም የውሃ ሀብትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ በትብብር ለመስራት፣ እውቀትን ለመለዋወጥ እና ተግባራዊ እቅዶችን ለማዘጋጀት እቅድ ያለው ነው ተብሏል።

በመድረኩ የአዘጋጅ ተቋማቶቹን ሀላፊዎች ጨምሮ ከተለያዩ ሴክተሮች የተውጣጡ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን ያሰባሰበ በአዋሽ ተፋሰስ ዘላቂ የውሃ አያያዝ አሰራር ላይ በመወያየት ስትራቴጂ ማዘጋጀት ተችሏል።



ተቋማዊ መድረኮች

የመውጫ ፈተና ውጤት ማሻሻል

በ2016 የተሻለ የመውጫ ፈተና ውጤት ለማስመዝገብ የተደረገ ውይይት።



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ካውንስል አባላት ተመራቂ ተማሪዎች በሚወስዱት የመውጫ ፈተና አፈፃፀም እና ውጤት ማሻሻል ላይ ያተኮረ ውይይት አድርጓል። ለውይይቱ መነሻ የ2015 ትምህርት ዘመን የመውጫ ፈተና አፈፃፀም እና የተመዘገበው ውጤት (65%) ሪፖርት እና የ2016 በጀት አመት እቅድ ቀርቧል።



በትምህርት ዘመኑ ለተመዘገበው ውጤት በዩኒቨርሲቲው የተሰሩ በርካታ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን በቀጣይ ክፍተቶችን በማረም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል አዲስ ሃሳብ እና አተገባበር ተይዞ ወደ ስራ እንደተባ ተገልጧል።



ተቋማዊ መድረኮች "የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲነት የሽግግር ፍኖተ ካርታ"

"የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲነት የሽግግር ፍኖተ ካርታ" ላይ የተዘጋጀ ወርክሾፕ

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ወደ ተግባር ዩኒቨርሲቲነት ለመሸጋገር የሚመራበት ፍኖተ ካርታ (Transition Roadmap towards a University of Applied Sciences) የመጀመሪያ ረቂቅ መጠናቀቁን አስመልክቶ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ግብዓት ለመሰብሰብ እና ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ ወርክሾፕ አካሂዷል።



መድረኩ "በኢትዮጵያ የተጀመረውን የትምህርት ፍኖተ ካርታ የፖሊሲ ለውጥን መነሻ በማድረግ እና ከትምህርት ጥራትና ፍትሃዊ ተደራሽነት አንፃር እና ተግባር ተኮር ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል ግልፅ ፍኖተ ካርታ እንዲሆን ግብዓት ለማሰባሰብ የተዘጋጀ ነበር።

ይህም ከተለያዩ አለም አቀፍ የትምህርት ተቋማት የተቀሰሙ ተሞክሮዎችን በመቀመር ያዘጋጀውን ፍኖተ ካርታ አፅድቆ በተግባር የታገዘ ትምህርት በመስጠት:የምርምር ስራወችን ወደ ማህበረሰብ በማውረድ ለአካባቢው ብሎም ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት በማለም ነው።



ተቋማዊ መድረኮች

የሴት ሰራተኞች ማህበር ምስረታ

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የሴት ሰራተኞች ማህበር ተመሰርቷል::

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የሴት ሰራተኞች ማህበር መመስረቻ ረቂቅ ደንብ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኃላ በሙሉ ድምፅ በማፅደቅ ሶስት አባላት ያሉት የማህበሩን ዋና አመራሮች በማስመረጥ ተመስርቷል ::

ማህበሩ በዋናነት ስርአተ ፆታን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ለማስፈጸም: የሴት የሰራተኞችን እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ :በተቋሙ የለውጥ ስራዎች ላይ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ እንዲሁም የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት አመች የሆነ አሰራርን ለመፍጠር በማለም መሆኑ ተገልጿል ::









ጉድኝቶች

ከክልሉ የእንስሳት ልማት ዘርፍ ቢሮ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሟል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከአፋር ክልል የእንስሳት ልማት ዘርፍ ከሰመራ እንስሳት ላብራቶሪ ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል ::





ስምምነቱ ለእንስሳት ጤና ባለሙያዎች የትምህርት እድልና ማመቻቸት፣ የጋራ የምርምር ፕሮጀክቶችን መቅረፅ እና መስራት፣ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን መስጠት፣ የጋራ የህክምና እና ክትባት ዘመቻዎችን ማድረግ፣ የቤተሙከራ መሳሪያዎችን እና የህክምና ግብአቶችን በጋራ መጠቀም የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር ያለመ ነው።

ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል።

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (EBC) በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል። ዩኒቨርሲቲው የአፋርን ባህልና ታሪክ በማጥናት፣ በማስተዋወቅ ክልሉን የባህል ቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ የጀመራቸውን ጥረቶች እውን ለማድረግ የሚጠቅም የመግባቢያ ስምምነት ነው።





የኢቲቪ በአፋርኛ ቋንቋ በሬድዮ ከ60 አመት በላይ፣ በቴሌቪዥን ደግሞ ከ15 አመት በላይ የሰራ በመሆኑ የህዝቡን ባህል በቅርበት የሚያውቅ ሚዲያ ሲሆን ስምምነቱ የክልሉን ህዝብ ባህል፣ወግ እና ትውፊቶች ለአለም በማስተዋወቅ እና ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል መልካም አጋጣሚ ነው::

ጉድኝቶችየህግ ትምህርት ቤት እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ማዕከል

የህግ ት/ቤት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ማዕከል ሥልጠና፣ ክርክር እና ፊርማ





የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ማዕከል ጋር የመግባቢያ የስምምነት ሰነድ ፊርማ በመፈራረም ሥልጠና እና በተማሪዎች መካከል ክርክር አካሂዷል።



ሥልጠናውን በተግባር ለማጠናከር ተማሪዎቹ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ ባተኮረ የመከራከሪያ ርዕሰ ላይ መምህራን እና ተማሪዎች በተገኙበት ሰፋ ያለ ክርክር አድርገዋል።

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና ራያ ዩኒቨርሲቲ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል።



ስምምነቱ በጋራ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶችን መስራት፣ የተቀናጀ የማኅበረሰብ አገልግሎት፣የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እና መሰል ዘርፎች ላይ በትብብር ለመሥራት ያለመ ነው።



ተቋማቱ የጋራ ፕሮጀክቶችን ቀርፀው ሲሰሩ ተመጋጋቢ ኢኮኖሚ ለመገንባት ከማስቻሉም በላይ ለማህበረሰብ ሰላም ግንባታ እንደሚጠቅም እና ቀጣይነት ያለው ስትራቴጂያዊ ትስስር ለመፍጠር ያስችላል።

ጉድኝቶች

የሳውዘርን ዴንማርክ ዩኒቨርሲቲ

የሳውዘርን ዴንማርክ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት እና ውይይት

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ከሳውዘርን ዴንማርክ ዩኒቨርሲቲ እና ኢስበርግ ኢኒሸቲቭ ግሩፕ ፎር ሪሊፍ ኤንድ ደቨሎፕመንት ከተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት የመጡ እንግዶችን ተቀብሎ በትብብር መስራት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት እና ጉብኝት ተደርጓል::

ልኡካኑ ከሠመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር ባደረጉት ውይይት፣ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና በአካባቢው ስላሉ አጠቃላይ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለማህበረሰብ አገልግሎት ምቹና አስፈላጊ ስለሆኑ በጥናት የተለዩ ጉዳዮችን ላይ ውይይት አድርገዋል።

በተጨማሪም ከህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን እና ከሁለተኛና የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ጋር መማር ማስተማር ላይ ያተኮረ ምክክር አድርገዋል።







ጉድኝቶች

የቻይናው MFA የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ

የቻይናው MFA የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ጋር ውይይት



የቻይናው MFA የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ XUE Bing ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት መሀመድ ኡስማን (ዶ/ር) ጋር በፅህፈት ቤታቸው በአጋርነት ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል።

በውይየት ወቅት ዶ/ር መሀመድ እንደገለፁት XUE Bing እና ቡድናቸው በዩኒቨርሲቲው ባደረጉት ጉብኝት በሰመራ ዩኒቨርሲቲ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ስራዎችን እና በትብብር መስራት የሚቻልባቸውን ጉዳዮች አብራርተዋል።

XUE Bing በተለይ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በትምህርት እድሎች ላይ አጋርነታቸውን ለመጀመር ያላቸውን ፍላጎት ገልፀዋል። ልዩ መልዕክተኛ በማስከተልም የሰመራ ዩኒቨርሲቲን የአለም አቀፋዊነት ጥረቶች እንደሚደግፉ አረጋግጧል። ሁለቱም ወገኖች በቻይና የሚገኙ ተቋማትን ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር በአጋርነት ማስተሳሰር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ውጤታማ ውይይት አድርገዋል።



ጉድኝቶች

በምስራቅ አፍሪካ ዩኒቨርስቲዎች የሶስትዮሽ አጋርነት

በምስራቅ አፍሪካ ዩኒቨርስቲዎች መካከል የሶስትዮሽ አጋርነት ስምምነት

የኡጋንዳው ማኬሬሬ ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ ሰመራ እና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የአካዳሚክ ልህቀት እና ፈጠራን ለማሳደግ ያለመ የሶስትዮሽ አጋርነት ፈጥረዋል።



የዩኒቨርሲቲዎቹ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በኢንቴቤ ከተማ ተገናኝተው በአካዳሚክ ፕሮግራሞች ልውውጥ፣ በምርምር፣ በአቅም ግንባታ፣ በኢንዱስትሪ አጋርነት እና በተማሪዎች ልውውጥ ላይ ያላቸውን ትብብር ለማሳደግ ተወያይተዋል።

ይህ አጋርነት በኡጋንዳ ኢንቴቤ የተካሄደውን 4ኛው የኢጋድ የትምህርት ጉባኤ ሚኒስትሮችን ተከትሎ የተካሄደ ውይይት ነው።



ሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስምምነት

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና የአፋር በሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የትምህርት እድል እንዲያገኙ የሚያስችል የስምምነት ተፈራርመዋል።

የስምምነቱ አላማ በክልሉ ያሉ የፍርድ ቤት ዳኞች በሚፈጠርላቸው እድል የትምህርት ደረጃቸውን ለማሻሻል ሲሆን ይህም ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ በክረምት እና በበጋ የትምህርት መርሃ-ግብር ይተገበራል።





ጉድኝቶች

የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የመግባቢያ ስምምነት

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በድንበር አስተዳደር፣ በሰላምና ፀጥታ እና ሰደትን በተመለከተ በትብብር ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል።

ስምምነቱ በዋናነት ሁለቱ ተቋማት፣ በመማር ማስተማር፣ ጥናትና ምርምር፣ በስልጠናና የአቅም ግንባታ ስራዎች፣ የምርምር ፕሮጀክትን በጋራ በመቅረፅ፣ የጥናት ውጤቶችን በመለዋወጥ እንዲሁም የተለያዩ አውደጥናቶችን በማዘጋጀት መስራትን እንደሚያጠቃልል ተገልጿል።



የ Erasmus+ ፕሮግራምን የተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ

በትምህርት ሚኒስቴር የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ኤባ ሚጀና በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ተገኝተው በኢራስመስ / Erasmus+ ፕሮግራም ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥተዋል።



የኢራስመስ /Erasmus+ በ27 የአውሮጳ ኅብረት ሀገራት ድጋፍ የተደራጀ በትምህርት፣ በስልጠና እውቀትን፣ ክህሎትንና ቴክኖሎጂን በተቋማት መካከል ልውውጥ እንዲኖር የሚደግፍ ትልቅ ፕሮግራም እንደሆነ ግንዛቤ ተፈጥሯል።

በዚህም ለምሁራኑም ሆነ ለዩኒቨርሲቲው የአቅም ግንባታ፣ የመማር ማስተማር፣ የምርምር በሮችን በመክፈት ብቃት ያለው የሰው ሀብት ለማፍራት እንደሚያስችል ተገልጿል ።



ጉድኝቶች

በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር በሠመራ ዩኒቨርሲቲ

በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር Shri Robert Shetkintong በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት

በኢትዮጵያ የሕንድ አምባሳደር Shri Robert Shetkintong በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት እና ከአመራሮች ጋር ውይይት አድርገዋል::

አምባሳደር ሮበርት በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኘውን ሎጊያ ሆስፒታልን እና ሬዶ የባህልና ሀገር በቀል እውቀቶች ጥናት ማእከልን ጎብኝተዋል::





የጉብኝቱ አላማ በጦርነት እና በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች የአካላዊ ተሃድሶ ድጋፍ ለመስጠት ያለመ ነው::

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ከኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች አገልግሎት (IPS) ጋር የመግባቢያ ስምምነት

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች አገልግሎት (Industry Projects Service) በትብብር ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል::





የስምምነቱ አላማ የተቋማቱን የካበተ እውቀት ፣ ከባለሙያዎች አቅም ጋር በማቀናጀት የጋራ የምርምር ፕሮጀክቶችን መቅረፅ ፣ አዋጭነታቸውን በማጥናት መስራትና ፣ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች በመስጠት፣ ችግር ፈቺ ጥናቶችን ወደ ኢንዱስትሪ ምርት በመቀየር የስራ እድል የሚፈጥሩ ስራዎችን በመስራት ህዝብን መጥቀም የሚያስችል እድል መፍጠር ነው ተብሏል::

ጉድኝቶች

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የአለም አቀፉ የፍልሰት

ዩኒቨርሲቲው ፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅትና ስምምነት



የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ክብርት ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ዶ/ር መሃመድ ኡስማን እና የዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት ተወካዮች መደበኛ ያልሆነ ፍልሰትን መቀነስ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ጋር ተወያይተዋል።

በውይይቱም ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተለይም ከአማራና ከትግራይ ክልል በህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎችና ደላሎች አማካኝነት አፋርን እንደመተላለፊያ ኮሪደር በመጠቀም ወደ ጂቡቲና የመን በመጨረሻም መዳረሻቸውን ሳውዲ አረቢያ የሚያደርጉ ወጣቶች፣ ሴቶችና ህጻናት ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የመከላከል እርምጃ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ሰመራ ዩኒቨርስቲ መደበኛ ያልሆነ ፍልሰትን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል የጥናትና የምርምር ክፍል በመክፈት ለህግና ለፖሊሲ አውጪዎች እንዲሁም በጉዳዩ ዙሪያ ጥልቀት ያለው የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለማካሄድ የበኩሉን እገዛ ያደርጋል።

የሚቺጋን ስቴት ፣ ሰመራ እና የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች የፕሮጀክት ማረጋገጫ (Validation) ወርክሾፕ

በሚቺጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ፣ በሰመራ እና በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ያለውን የአካዳሚክ አጋርነት ለማጠናከር የፕሮጀክት ማረጋገጫ አውደ ጥናት በአዲስ አበባ ተካሄዷል።

የአሜሪካ ኤምባሲ በኢትዮጵያ የገንዘብ ድጋፍ የተደረገው ይህ አጋርነት ሥርዓተ ትምህርትን ለማጎልበት እና በእንስሳት መኖ እና ስነ-ምግብ ትምህርት እና ምርምር ተቋማዊ አቅምን ለማጠናከር ያለመ ነው።





ትብብሩ በኢትዮጵያ የትምህርት እና የግብርና ዘርፉን ለማሳደግ የሚተገበር ፕሮጀክት ነው። መድረኩ የሁሉንም ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፣ ባለሙያዎችን እና ባለድርሻ አካላትን በማሰባሰብ ፕሮጀክቱን መገምገም እና አጋርነታቸውን የበለጠ ለማጠናከር የቻለ መሆኑ ተመላክቷል።

ጉድኝቶች

የአቅም ግንባታ የክትትል የመክፈቻና የመነሻ ውጤት ስርጭት መርሃ ግብር

የአቅም ግንባታ የክትትል መርሃ ግብር የመክፈቻና የመነሻ ውጤት ስርጭት አውደ ጥናት

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የአፋር ክልል ጤና ቢሮ፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በትብብር የአቅም ግንባታ ክትትል መርሃ ግብር የከፈቱ ሲሆን የጤና መረጃ ስርዓት Health Information System (HIS) ማስጀመሪያና የዳሰሳ ጥናት ውጤት ስርጭት አውደ ጥናት በአፋር ክልል ሰመራ ከተማ አካሂደዋል።



የአቅም ግንባታና ክትትል ፕሮግራም Capacity Building Monitoring Program (CBMP) የዳሰሳ ጥናት ውጤትን መሰረት በማድረግ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በክልሉ የተመረጡ ሞዴል ወረዳዎችን በመፍጠር የቴክኒክ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።



ይህ ተነሳሽነት የጤና መረጃ ስርዓቱን ወደ ዲጂታላይዜሽን ከማሳደግ በተጨማሪ ለዩኒቨርቲው ተማሪዎች ተግባራዊ የጤና ሳይንስ ልምድን የሚሰጥ እንዲሁም የሴቶችን እና የጤና ባለሙያዎችን አቅም የሚገነባ ነው።



ጉድኝቶች

የኤስኤአይዲ ምላሽ አመራር ተግባር በአፋር ክልል የDRM የበጎ ፈቃደኞች

USAID የ አደጋ ስጋት ምላሽ አመራር ተግባር በአፋር ክልል የDRM የበጎ ፈቃደኞች ስልጠና

USAID የ አደጋ ስጋት ምላሽ አመራር ተግባር ከአፋር ክልል ከባለድርሻ አካላት ጋር ስልጠና፣ ቁጥጥር እና ውይይት አካሂዷል። ፕሮጀክቱ በአደጋ ስጋት አስተዳደር የበጎ ፈቃድ ቡድን ስልጠና ለ35 ከማህበረሰብ ለተወጣጡ ተሳታፊዎች በማቀድ፣ በማዘጋጀት እና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚደርሱትን ማንኛውንም የአደጋ ስጋቶች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስልጠና ሰጥቷል።



ከፕሮጀክቱ፣ ከሠመራ ዩኒቨርሲቲ እና አጋር ድርጅቶች የተውጣጡ የቁጥጥር አባላት ከአፋር ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊዎች እና ከፍተኛ አመራሮች ጋር ተወያይቷል፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና የአፋር ክልል የአደጋ ስጋት ሰራ አመራር ኮሚሽን በክልሉ የሚከናወኑ የፕሮጀክት ስራዎችን በማስተባበር ይቆጣጠራል።



ድጋፍ

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ለራያ ዩኒቨርሲቲ ድጋፍ አድርጓል።



ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ራያ ዩኒቨርሲቲን መልሶ ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ እና አብሮነትን በተግባር ለመግለፅ ያለመ ከ1.8 ሚሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው ቁሳቁሶችን ድጋፍ አድርጓል።



ጉብኝቱ ሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ ለመስራት የተፈራረሙትን የመግባቢያ ስምምነት ወደ ተግባር ለመቀየር እንዲሁም በጋራ የምርምር እና ማህበረሰብ ተኮር ፕሮጀክቶችን ለመቅረፅ በሰፊው የተመካከሩበት እና ውሳኔዎችን ያሳለፉበት ነው።



ድጋፍ

ሞተር ሳይክሎች ቁልፍ ርክክብ

በረጅም ጊዜ ክፍያ ለአመራሮች የተገዙ ሞተር ሳይክሎችን ቁልፍ ርክክብ



ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ለመካከለኛ አመራሮች በረጅም ጊዜ ክፍያ የሚጠናቀቁ 30 ሞተር ሳይክሎችን በተቋሙ ውስጥ ገቢ በኩል ገዝቶ ዶ/ር መሀመድ ኡስማን (ፕሬዚዳንት) እንዲሁም ሁሉም ምክትል ፕሬዝዳንቶች በተገኙበት ቁልፍ አስረክቧል::





ድጋፍ ለሴት ተማሪዎች

ለሴት ተማሪዎች የተለያዩ የመገልገያ ግብአቶች ድጋፍ

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ በህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህር እና የስርዓተ ፆታ አስተባባሪ የሆኑት ወ/ሮ መድና ሁመድ አስተባባሪነት ከአፋር ክልል ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በመተባበር ድጋፍ አድርገዋል።

ከድጋፉ በተጨማሪ ሴት ተማሪዎች በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት በማስመዝገብ ተወዳዳሪዎች እንዲሆኑ በስነ-ልቦና ተነሳሽነት ዙሪያ የምክር አገልግሎት





ለ150 ሴት ተማሪዎች ከ450 ሺ ብር በላይ የሚገመት መገልገያ ቁሳቁስ የንፅህና መጠበቂያ ግብአቶችን ጨምሮ ድገፍ ተደርጓል።



ማህበረሰብ አገልግሎት

ሰመራ እና ወልዲያ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ህክምና ፕሮጀክት አስጀምረዋል::

ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ህክምና ፕሮጀክት(Mobile Veterinary Project) በአፋር ክልል በጭፍራ ወረዳ ወእማ አካባቢ ላይ በመገኘት አካሄደዋል::

ሁለቱ አጎራባች ዩኒቨርሲቲዎች የአፋር እና አማራ ክልል በሚዋሰኑበት አካባቢ የሚኖሩ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ እንስሳትን እስከ መኖሪያ ቀያቸው ድረስ በመሄድ የክትባት እና የጠቅላላ ህክምና አገልግሎቶችን በመስጠት: ማህበረሰቡ ከእንስሳቱ ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኝ ማስቻል ነው::



ፕሮጀክቱ በገበያ እና በግጦሽ ሁል ጊዜ ስለሚገናኙ እና ለተላላፊ በሽታዎች ተጋላጭ ስለሚሆኑ ከህክምና ይልቅ መከላከል ክትባት ላይ አመላክቷል::



ማህበረሰብ አገልግሎት

የአፋር ታለንት አካዳሚ

የአፋር ታለንት አካዳሚ የመጀመሪያ ዙር ተማሪዎቹን የመግቢያ ፈተና ሰጥቷል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ባደረጉት ስምምነት የተመሰረተው የአፋር ታለንት አካዳሚ የመጀመሪያ ዙር ተማሪዎቹን ተቀብሎ የመግቢያ ፈተና መስጠቱን ተገልጿል::



የመግቢያ ፈተናውን የወሰዱት በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የ8ተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ያስፈተኑ ትምህርት ቤቶች 900 የሚሆኑ ተማሪዎች ተመዝግበው አካደሚው በ2016 ትምህርት ዘመን ማጣሪያውን የሚያልፉትን 100 ተማሪዎች ያስተምራል። የመግቢያ ፈተናው የሚሰጥባቸው የትምህርት ዓይነቶች አፋርኛ ቋንቋ ፣ እንግሊዝኛ: ሒሳብ እና አጠቃላይ ሳይንስ መሆናቸው ተጠቁሟል።

የአፋር ታለንት አካዳሚ ዓላማ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸው: በስነ-ምግባራቸው የላቁ : በትምህርታቸው በሀገር እና በአለም አቀፍ መድረኮች ተወዳዳሪ: ቤተሰብን ብሎም ሀገርን የሚያኮሩ ተማሪዎችን ማፍራት ነው::



ማህበረሰብ አገልግሎት

ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ኮሚሽን የቁሳቁስ ድጋፍ

ዩኒቨርሲቲው ለአፋር ክልል ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ኮሚሽን የቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል።

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ የመገልገያና የቢሮ ቁሳቁሶችን ለአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ኮሚሽን ድጋፍ አድርጓል::

ከተሰጡት ንብረቶች ውስጥ ፍራሽ:ፋን:ወንበርና ጠረንጴዛ እንዲሁም ደስክቶፕ ኮምፒዩተሮች መሆነናቸው ተገልጸዋል::



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በማህበረሰብ አገልግሎት ሰራዎቹ በየአመቱ በክልሉ ለሚገኙ የተለያዩ ተቋማት የሙያና የቁሳቁስ ድጋፍ ያደርጋል::



ማህበረሰብ አገልግሎት

እፅዋትን መንከባከብ እና ጽዳት

አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት-እፅዋትን መንከባከብ እና ጽዳት

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ የመገልገያና የቢሮ ቁሳቁሶችን ለአፋር ብሄራዊበየአመቱ የሚካሄደው የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት "የጽዳት እና እፅዋትን የመንከባከብ ቀን" በሰመራ ከተማ በፅዳት እና ችግኞችን በመንከባከብ ተጀምሯል።



የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት መርሀ-ግብር ባህል ሆኖ እንዲቀጥል እና በክልሉ የሚገኙ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህን አርአያ የሆነ ተግባር ወስደው ማህበረሰቡን በጋራ ማገልገል የሚያስችል ግንዛቤ የመፍጠር አላማን ያነገበ ዘመቻ መሆኑ ተገልጿል።



ማህበረሰብ አገልግሎት

"የትምህርትና ነፃ የህግ አግልግሎት ቀን"

"የትምህርትና ነፃ የህግ አግልግሎት ቀን" በሰመራና ሎጊያ ከተሞች

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት ሁለተኛ ቀን በሰመራና ሎጊያ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች እንድሁም በሰመራ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትበተለያዩ ተግባራት አከናውኗል::



የፕሮግራሙ አላማ ማህበረሰቡን በተግባር ማገልገል በመሆኑ በትምህርት ላይ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለመደገፍ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ክፍለ ጊዜ ወስደው በማስተማር የማነቃቃት እና መምህራን የማገዝ ስራ አከናውነዋል::

በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ውጤታማ የአጠናን ዘዴ በተመለከተ የዩኒቨርሲቲው የሳይኮሎጂ መምህራን ሰፊ ትምህርት እና ገለፃ አድርገዋል::

በመጨረሻም ከመምህራን በተውጣጣ ገንዘብ የተገዙ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ለተመረጡ ተማሪዎች ተደርጓል::





ማህበረሰብ አገልግሎት

"የጤና ቀን"

አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት "የጤና ቀን" በተለያዩ ተግባራት ተከብሯል።

አመታዊውን የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት "የጤና ቀን"ን ምክንያት በማድረግ የደም ልገሳ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ፣ተንቀሳቃሽ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት በሰመራና ሎጊያ መካከል በሚገኙ አካባቢዎች የተሰጠ ሲሆን: ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች መሰረታዊ የጤና አጠባበቅ ስልጠና ተሰጥቷል።





የምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ፅ/ቤት:የህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና የእንስሳት ህክምና ኮሌጅ ጋር በመተባበር ተዘጋጂቶ የዩኒቨርስቲ ማኅበረሰብ ደም ለግሰዋል።



ማህበረሰብ አገልግሎት

"የጤና ቀን"

“የጤና ቀን” በዱብቲ ሆስፒታል ታካሚዎችን በመጠየቅ ተጠናቋል።

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2016 የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት “የጤና ቀን” በመሰረታዊ የጤና አጠባበቅ ስልጠና የተከናወነበት ሲሆን: በዱብቲ ሆስፒታል ህሙማንን በመጠየቅ፣ በመንከባከብ እና ድጋፍ በማድረግ ተጠናቋል።





ከ250 ሺ ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የተለያዩ የህክምና ቁሳቁሶች እና በቀጥታ ለህሙማን የሚሰጡ አልባሳት እና ምግብ ነክ ድጋፎች የተበረከተ ሲሆን ድጋፉንም የዩኒቨርስቲው ከፍተኛ አመራሮች ሰጥተዋል።



ማህበረሰብ አገልግሎት

"የቱሪዝም ቀን" እና "እድዋን"

"የቱሪዝም ቀን" እና "እድዋን" በ"አላሎበድ" ድንቅ የተፈጥሮ ፍል ውሃ

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት 4ኛ ቀን "የቱሪዝም ቀን" እና በየአመቱ የካቲት 23 የሚከበረው 128ኛው የአድዋ ድል መታሰቢያ በአል ከሰመራ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው "አላሎበድ" ድንቅ የተፈጥሮ ፍል ውሃ ጉብኝት በማድረግ አክብሯል።





የጉብኝቱ አላማ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዙሪያቸው ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች እንድያውቁ፣መስህቦችን እንዲያደንቁ እና ለምርምር የሚሆን ግንዛቤን እንድወስዱ በማሰብ ነው ሲሉ የቱሪዝም እና የጂኦ ቱሪዝም ትምህርት ቤት ምሁራን ተናግረዋል።

የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣መምህራን፣ ሰራተኞች እና ተማሪዎች እንድሁም የክልሉ የቱሪዝም ቢሮ የስራ ሀላፊዎች በጉብኝቱ ተሳትፈዋል።



ማህበረሰብ አገልግሎት

ተመራቂ ተማሪዎች የፅዳት ዘመቻ

የ2016 ትምህርት ዘመን ተመራቂ ተማሪዎች የፅዳት ዘመቻ አካሄዱ::

በተለያዩ የትምህርትመስኮችዳትእናየተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት ሀላፊዎችን ባሳተፈ የፅዳት ዘመቻ ግቢያቸውን በጋራ አፅድተዋል።

የዩኒቨርስቲው ፕሬዚደንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን እና ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተመራቂ ተማሪዎች "ውለታ ለዩኒቨርሲቲዬ" በሚል መሪ-ቃል የፅዳት ዘመቻ አድርገዋል።





እጩ ተመራቂ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው በሚቀጥለው አመት ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች ግቢያቸውን ውብና ጽዱ በማድረግ እንዲወጡ በማሰብ የአርያነት ሥራ መስራታቸውን ገልጸዋል።



ማህበረሰብ አገልግሎት ዩኒቨርሲቲው ለአላሎበድ አካባቢ ማህበረብ ድጋፍ

ዩኒቨርሲቲው ለአላሎበድ አካባቢ ማህበረብ መነቃቃት የበኩሉን ድጋፍ አድርጓል::

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በማህበረሰብ አገልግሎት ስራው ለአላሎበድ አካባቢ ማህበረብ መነቃቃት አስተዋፅኦ ያላቸውን በትምህርት፡ በቱሪዝምና በስራ ፈጠራ የሚያግዙ የቁሳቁስና የሙያ ድጋፎችን ማድረጉ ተገልጿል::



ዩኒቨርሲቲው የተማረ ዜጋን ከማፍራት በተጨማሪ አመቱን ሙሉ በሚሰራቸው የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎቹ ለበርካታ የክልሉ ተቋማትና የማህበረሰብ ክፍሎች የሙያና የቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል::

ለአላሎበድ አስጎብኝዎች ማህበር የጎብኝዎች ማረፊያ ለመስራት የሚውል የጣሪያ ቆርቆሮና ምስማር:የምግብ ማብሰያ በርሜሎችን: ለመኝታ አገልግሎት የሚውሉ አልጋዎችንና ችፑድ የትራስና የአልጋ ልብሶችን አበርክቷል::



ማህበረሰብ አገልግሎት

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ከICARDA ከተባለ ግብረሰናይ ድርጅት ጋር

ማህበረሰብ ኑሮ የሚያሻሽሉ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ከ***ICARDA*** ከተባለ ግብረሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር በ***2015*** የአፋር ፍየል ዝርያ ማሻሻያ ፕሮጀክት ***(Community Based Goat Breeding Project)*** በአይሳኢታ ወረዳ በ***3*** መንደሮች የተመረጡ የፍየል ኮርማዎችን ገዝቶ ለአርብቶ አደሮች በመስጠት ያስጀመረውን የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራ በማስቀጠል ከመጋቢት ***26*** እስከ ሚያዚያ ***07/2016*** ድረስ መሠረታዊ መረጃ የመሰነድ ስራ ማከናወኑን ገልጿል።

የማህበረሰብ አቀፍ የአፋር ፍየል ዝርያ ማሻሻያ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ የአርብቶ አደሩን ገቢ ማሻሻል የሚችሉ ፍየል ዝርያዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው።



የመረጣ እና የማዳቀል ዘዴን ከነባሩ የማህበረሰብ ልምድና እውቀት ጋር በማቀናጀት ተፈጥሮአዊ አቅማቸውን በማሳደግ ጥሩ የውልደት መጠንና የእድገት ደረጃ ያላቸው የተሻለ የስጋ ምርት የሚሰጡ የፍየል ዝርያዎችን ማብዛት እንደሆነ ተጠቁሟል።



ማህበረሰብ አገልግሎት

የሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ

በክልሉ የሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ማስጀመሪያ ፕሮግራም ተካሄዷል::

የኢፌዲሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፡ የህንድ ኤምባሲ በኢትዮጵያና የህንድ መንግስት፡ ከሠመራ ዩኒቨርሲቲ፡ ከአፋር ክልል ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በትብብር የሚያካሂዱት የሰው ሰራሽ የእጅ እና የእግር ድጋፍ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የሚሰጠውን አገልግሎት የማስጀመሪያ መርሃግብር በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሎጊያ ሆስፒታል ተካሂዷል::





አገልግሎቱን ከህንድ የመጡ **8** የህክምና ባለሙያዎች ቅድሚያ ለተመዘገቡ **400** ለሚሆኑባገብወገኖች እንዲሁም በሚቀጥሉት **50** ቀናት አገልግሎቱን ፈልገው ለሚመጡ ሰዎች እንደሚሰጥ ተገልጿል::







ማህበረሰብ አገልግሎት

በአብአላ የኤክስቴንሽን ማዕከል

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በአብአላ የኤክስቴንሽን ማዕከልን ጎበኙ::

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ ትምህርትን ለክልሉ ማህበረሰብ ለማድረስ በሚያደርገው ጥረት ከዋናው ግቢ በተጨማሪ **5** የኤክስቴንሽን ማዕከላትን በአይሳኢታ፣ ባቲ፣ አዋሽ(ወረር)፣ አብአላ እና ጭፍራ በመክፈት ዜጎች የቦታ ርቀት ሳይገድባቸው እንዲማሩ እያደረገ ይገኛል::

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን : ከርቀትና የተከታታይ ትምህርት ክፍል ዳይሬክተር አቶ ኢስማኢል ጋር በመሆን በአብአላ የኤክስቴንሽን ማስተማሪያ ማዕከልን የጎበኙ ሲሆን ከተማሪች ጋር በሚሰጠው የትምህርት አገልግሎት ዙሪያ ውይይት አድርገዋል::



በዞን-**2** ሰባት ወረዳዎችን እንዲያስጠቅም ታስቦ የተከፈተው ማእከሉ የብዙዎችን የትምህርት ፍላጎት ያነቃቃ መሆኑም ተገልጿል::



የምርምር ሥራዎች

Climate Smart Practice Begins in the Tigray-Afar Border በትግራይ-አፋር ድንበር

PENHA-TBI ፕሮጀክት በትግራይ-አፋር ድንበር (TAB) የአየር ንብረት ማሻሻያ ሰራዎችን ጀምሯል:: የፕሮጀክቱ አላማ ለሁለቱ ክልሎች ምርታማ የሆነ የመሬት አቀማመጥን መልሶ እንዲያገግም በማስቻል የደረቀ መሬትን መልሶ ማልማት:ገበሬውን እና ሴቶችን ያማከለ የደን ልማት እና የሰላም ግንባታን ያካተተ ነው::





ጥምረቱ TBI፣ Tigray BoANR፣ CIFOR-ICRAF፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ፣ የትግራይ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና የትግራይ ባዮቴክኖሎጂ ማዕከልን ያጠቃልላል። በማስጀመሪያ መርሃግብሩ ላይ የአጋር ተቋማት ተወካዮች እና ፕሮፌሰር. ምትኩ ኃይሌ (የአፈር ሳይንቲስት)፣ ከአብአላ እና እንደርታ አካባቢዎች አመራሮች፣ ተጠቃሚዎች እና የአገር ሽማግሌዎች ተሳትፈውበታል።



ምርምር ሥራዎች

ዓመታዊ የቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮፖዛሎች ግምገማ

ዓመታዊ የቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮፖዛሎች ግምገማ ወርክሾፕ ተካሄዷል።

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ቴክኖሎጅ ሽግግር ም/ፕሬዝደንት ጽህፈት ቤት ዓመታዊ የቴክኖሎጂ ምርምር ፕሮፖዛሎችን መገምገሚያ ወርክሾፕ አካሂዷል።



በወርክሾፑ ሰባት ፕሮፖዛሎች ለግምገማ ቀርበው በምሁራን ተተችተው: ሃሳብ እና አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል ።

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን የምርምር ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ተቀይረው የህዝቡን ኑሮ በተጨባጭ ለማሻሻል የሚያግዙ እንዲሆኑ ታቅዶበት እየተሰራ መሆኑን ተገልፀዋል ።



ምርምር ሥራዎች የግብርና የምርምር ስራዎችን የመስክ ምልከታ

በምርምር ሂደት ላይ ያሉ የግብርና የምርምር ስራዎችን የመስክ ምልከታ-በአይሳኢታ እና ዱብቲ

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በአይሳኢታ እና ዱብቲ በምርምር ሂደት ላይ ያሉ የግብርና የምርምር ስራዎችን የምርምር እና ቴክኖሎጅ ሽግግር ተ/ም/ፕሬዝደንት አደም አሊ ከተመራማሪዎች ጋር በመሆን የመስክ ምልከታ አድርገዋል::



በአሁኑ ሰአት ዩኒቨርሲቲው በድምሩ 166 ምርምሮችን እያካሄደ ሲሆን፡ ከእነዚህም ዉስጥ 7-ሜጋ፣ 3-ላርጅ፣ 46-ሚድ እና 110-ሚኒ ስኬል ምርምሮች ናቸው::



ከልህቀት መስኮች ውስጥ አንዱ በሆነው ግብርና ላይ እየተሰሩ ያሉ በሁለት አመት የሚጠናቀቁ 5 ሚድ ስኬል (mid-scale) ምርምሮችን የመስክ ምልከታ ተደርጎባቸዋል::

ዩኒቨርሲቲው ባህላዊውን አሰራር ይተካሉ ብሎ እምኖባቸው እየሰራቸው ከሚገኙት የግብርና ምርምሮች ውስጥ: 1. የተለያዩ አዝእርቶች የዘር ማሻሻል፣ 2.የማዳበሪያ ተገቢነት ሙከራ 3.የዘር ብዜት መጠንና ስርጭት፣ 4.የአዝእርት በሽታና ፀረ-ተባይ መድሀኒት ቁጥጥር ላይ ያተኩራሉ ::

ዩየአይሳኢታ እና ዱብቲ የምርምር ጣቢያዎችን ጨምሮ በተለያዩ የምርምር ቦታዎች በመጠናት ላይ ከሚገኙ የአዝእርት አይነቶች ውስጥ 5 አይነት የስንዴ፣5 አይነት የቦሎቄ እና 4 አይነት የቦቆሎ ዝርያወች ሲሆኑ፣ሞሪንጋ/ሽፈራው እና በተለምዶ የወያኔ ዛፍ እየተባለ የሚጠራውን የእፅዋት አይነት ለፀረ-ተባይ መድሀኒት ምርምር እየተደረገበት እንደሆነ ተጠቅሷል::



ምርምር ሥራዎች

የኮምፒውተር ሳይንስ ተማሪዎች ፕሮጀክት ኤግዚቢሽን

የኮምፒውተር ሳይንስ 3ኛ እና 4ኛ ዓመት ተማሪዎች ፕሮጀክት ኤግዚቢሽን

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት ክፍል የምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት UIL&TT ዳይሬክቶሬት በትብብር ያዘጋጁት የ3ኛ እና የ4ኛ ዓመት የኮምፒውተር ሳይንስ ተማሪዎችን የፈጠራ ፕሮጀክቶች የሚያሳይ ኤግዚቢሽን ተካሄዷል::





በኤግዚቢሽኑ የተማሪዎችን የቴክኒክ ብቃት እና የመፍትሄ ሃሳብ የማመንጨት አቅማቸውን የሚያሳዩ 10 የኮምፒውተር ሲስተሞችን አቅርበዋል::



University Level First Round Seminar Presentation Review Workshop

ምርምር ሥራዎች

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የመጀመሪያ ዙር ሴሚናር አቀራረብ መገምገሚያ አውደ ጥናት

በአውደጥናቱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና አስተዳደር፣ ጤና፣ ቋንቋ፣ ቴክኖሎጂ እና ሰነ-ህይወትን ያካተቱ አምስት የምርምር ፕሮጀክቶች ቀርበዋል።

በዚህ የምርምር፣ ሕትመት፣ ሰነ-ምግባርና ስርፀት ዳይሬክቶሬት ባዘጋጀው አውደጥናት በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ ተመራማሪዎች የምርምር ስራቸውን ጥራት የሚያጎለብቱበት የእውቀትና ልምድ ልውውጥ መድረክ እንደፈጠረ ተገልጿል።

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዝዳንት ጽህፈት ቤት: የእውቀት ሽግግርን ማጎልበት እና የምርምር ግኝቶችን ወደተግባር የመቀየር አላማን ያነገበ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የመጀመሪያ ዙር ሴሚናር አቀራረብ ግምገማ አውደ ጥናት አካሂዷል።















ምርምር ሥራዎች 7ኛው አመታዊ የምርምር ውጤቶች ማሳወቂያ አውደ ጥናት

7ኛው አመታዊ የምርምር ውጤቶች ለማህበረሰብ ማሳወቂያ አውደ ጥናት

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ባለፉት ሁለት አመታት የተሰሩ የምርምር ውጤቶችን በዘርፉ ምሁራን እና በባለድርሻ አካላት በማስገምገም የሚሰጡ ግብረ መልሶችን አካቶ ወደ ተግባር ለመቀየር የተዘጋጀ አውደ ጥናት ነው።

በአውደጥናቱ በውሃ ልማት፣ በጠቅላላ ግብርና፣ በጤና እና በማእድን ዘርፎች ላይ የተሰሩ 8 የምርምር ሥራ ውጤቶች ቀርበዋል::





በመድረኩ ለቀረቡት የምርምር ውጤቶች ቅርበት ያላቸው የክልል ፣ የዞን እና የወረዳ መስሪያ ቤቶች ተወካዮች የዩኒቨርሲቲው ምሁራን የተሳተፉ ሲሆን ፣ ይህም የምርምር ስራ ውጤቶችን ከማስተዋወቅም በላይ ገንቢ ግብዓ የተገኘበት መሆኑ ተገልጿል።



ምርምር ሥራዎች

የምርምርና የቴክኖሎጂ ስራ ውጤቶች ማሳያ አውደጥናት

የምርምርና የቴክኖሎጂ ስራ ውጤቶች ማሳያ አውደጥናት ተካሂዷል::

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የኢንዱስትሪ ትስስርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ተመራማሪ መምህራንን እና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች ፕሮፖዛሎች በማወዳደርና በመደገፍ ያሰራቸውን ያለቀላቸው የቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶች ማሳያ አውደ ጥናት አካሂዷል።





በአውደ ጥናቱ አራት የቴክኖሎጂ የምርምር ስራዎች መካከል በቻርጅ የሚሰራ ብስክሌት፣ በቤት ውስጥ በቀላሉ ሊሰራ የሚችል የመጠጥ ውሃ ማጣሪያ፣ የፀረ-ተባይ መከላከያ እንዲሁም የበቆሎ ምርት መፈልፈያ ማሽን ይገኙበታል::



ምርምር ሥራዎች

ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበው የአፋርአፍ የድህረ-ምረቃ ጥናታዊ ጽሁፍ

ለመጀመሪያ ጊዜ የአፋርኛ ቋንቋ የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሁፍ

የአፋርኛ ቋንቋ የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ትምህርት ክፍሉ ከተከፈተ ለመጀመሪያ ጊዜ የሆነውን የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሁፋቸውን አቅርበዋል:: የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሁፎቹን የትምህርት ክፍሉ መምህራን፣ ከክልል የአፋርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ማዕከል እንድሁም የግቢው ማህበረሰብ በተገኙበት ግምገማ ተደርጓል።





ለቋንቋውም ሆነ ለሰመራ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ የሆነው ይህ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም በመጀመሪያ ዙር በሁለት መስኮች Applied linguistics and communication እና Applied linguistics and teaching 11 ተማሪዎችን በማስተማር ለማስመረቅ በቅቷል።



ምርምር ሥራዎች

Daagu International Journal of Basic and Applied Research (DIJBAR)

Daagu International Journal of Basic and Applied Research (DIJBAR) እ

የዳጉ ኢንተርናሽናል ጆርናል ኦፍ ቤዚክ ኤንድ አፕሊይድ ሪሰርች Daagu International Journal of Basic and Applied Research(DIJBAR) ጥራዝ 6፣ ቁጥር 1 (2024) ህትመቱን አስነብቧል። ጆርናሉ በተለያዩ ዘርፎች እውቀትን እና ምርምርን ለማሳደግ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ተብሏል::

ይህ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጆርናል በ2012ዓ.ም የመጀመሪያ እትሙን ያስነበበ ሲሆን: በ2015ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና ተሰጥቶት ለተመራማሪዎች የምርምር ስራቸውን አሳትመው ለሌሎች እንዲያካፍሉ ወሳኝ መድረክ ሆኗል።

ጆርናሉ ባሉት ትጉህ ተመራማሪዎች፣ ገምጋሚዎች፣ አርታኢዎች እና አንባቢዎች እየተደገፈ ለአካዳሚክ ማህበረሰቡ ፈጠራን ምርምርን በማበረታታት ረገድ አስተዋፅዖ እያደረገ ይገኛል::



ADDITIONAL STRUCTURE

EDITORIAL TEAM

CONTACT JOURNAL

ORDER JOURNAL

ምርቃት-Graduation Cermony

የ2016 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች በደማቁ አስመርቋል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በ2016 ትምህርት ዘመን በተለያዩ የትምህርት መስኮች ያስተማራቸውን 1ሺ 478 ተማሪዎች አስመርቋል።



ከተመራቂ ተማሪዎቹ መካከልም 450 ሴቶች እና 1ሺ 28 የሚሆኑት ወንዶች ናቸው:: ዩኒቨርሲቲው በ38 የቅድመ-ምረቃ እና በ15 የድህረ-ምረቃ ፕሮግራሞች በድምሩ በ53 ፕሮግራሞች፣ በ3 መርሃ-ግብሮች (መደበኛ:ኤክስቴንሽን እና በርቀትና ተከታታይ) ያስተማራቸውን ተማሪዎች ነው ያስመረቀው::

የቱሪዝም ሚኒስተር ዲኤታ እና የዩኒቨርሲቲው የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ስለሸ ግርማ: በልህቀት መስኮች ላይ የተመዘገበው 53% የመውጫ ፈተና ስኬት ተጠናክሮ እንድቀጥል ሲሉ በአፅንኦት ተናግረዋል::



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ባደረጉት ንግግር እንደገለፁት ትምህርት ሚኒስቴር ከያዛቸው የሪፎርም ሰራዎች መካከል የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚሰጠውን የመውጫ ፈተና በከፍተኛ ውጤት 93% በማለፍ አኩርታችሁናል ብለዋል::





ምርቃት

የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች ምረቃ

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በአመቱ አጋማሽ ላይ በቅድመ ምረቃ መርሀ-ገብር 461 ተማሪዎችን አስመርቋል ::

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በአመቱ አጋማሽ ላይ በቅድመ ምረቃ መርሀ-ገብር ያስተማራቸውን 461 ተማሪዎችን አስመርቋል:: በምረቃው ላይ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን እንድሁም ዶክተር ኮንቴ ሙሳ በክብር እንግድነት በተገኙበት ተማሪዎቹ ተመርቀዋል::





በዚህ በአመቱ አጋማሽ ላይ ከተመረቁት ተማሪዎች መካከል 34ቱ በሀገር አቀፉ የመውጫ ፈተና 100% ያለፉ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ የመውጫ ፈተና በድጋሚ ወስደው ያለፉ ተማሪዎች ናቸው ::



ምርቃት ከብራይተር ጀነሬሽን ጋር በመተባበር የተማሩ ተማሪዎችን ምርቃ

ከብራይተር ጀነሬሽን ጋር በመተባበር በክረምት የሰለጠኑ ተማሪዎች ምረቃ::



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፣ ብራይተር ጀነሬሽን ከተባለ ግብረሰናይ ድረጅት ጋር በመተባበር ባሳለፍነው ክረምት ለአስር የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ልዩ ስልጠና ሰጥቷል።

ትምህርቱ እየርላንድ እና እንግሊዝ ሀገር በሚኖሩ በጎ ፈቃደኛ ዲያስፖራ መምህራን በበይነ-መረብ፣ በእንግሊዝኛ የተሰጠ ሲሆን፣ የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ኢንደስትሪ ትስስርና ቴክኖሎጅ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና የአይሲቲ መምህራን በማስተባበር አሰልጥነው በማብቃት አስመርቀዋል።

ስልጠናው በዋናነት የተማሪዎቹን አቅም ያገናዘቡ፣ለወደፊት የትምህርት እና የስራ ዘመናቸው መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ፣በህዝብ ፊት ንግግር የማድረግ ጥበብ፣የንባብ ክህሎት፣የመጻፍ ክህሎት፣በጥልቀት ማሰብ እና የአመራር ጥበብ ላይ ያተኮረ ነው።



አቅም ግንባታ

ለመምህራን የአሰልጣኞች ስልጠና

የአሰልጣኞች ስልጠና ለዩኒቨርሲቲው መምህራን ተሰቷል::

Dereja.com ከተለያዩ ኮሌጆች ለተውጣጡ 22 መምህራን በተቀጣሪነት እና ስራ ዝግጁነት ላይ ያተኮረ የአሰልጣኞች ስልጠና ሰጥቷል። የስልጠናው አላማ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በእውቀት እና በራስ የመተማመን ስነ-ልቦና በማነፅ የተሟላ የስራ አመለካከት ይዘው እንዲመረቁ እና በስራ አለም ላይም ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል ነው::



የምርምር አቅም ማጎልበቻ የEpi -info and STATA መተግበሪያዎች ስልጠና

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለማስተርስ ተማሪዎች "የምርምር አቅም ማጎልበቻ" ስልጠና ሰጥቷል:: ዓላማውም ተመራቂዎቹ ወደ ምርምር ሥራ ከመግባታቸው በፊት የምርምር ጽንሰ ሀሳብ እና መተግበሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን መተንተንና ውጤት ማቅረብ እንዲችሉ ማገዝ ሲሆን: የምርምር ምንነት፣ናሙና አወሳሰድ ፣ መረጃ አሰባሰብ ዘዴና ትንተና ፤ የምርምር ውጤት አቀራረብ እና ውስብስብ መረጃዎችን መተንተን የሚያስችሉ Epi -info and STATA የተባሉ መተግበሪያዎች አጠቃቀም በተግባር ሰልጥነዋል::



አቅም ግንባታ

ToT on Computer stream and Electronics stream

Computer stream እና Electronics stream የአሰልጣኞች ስልጠና

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ከ STEM POWER ጋር በመተባበር በComputer stream እና Electronics steam ላይ ያተኮረ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል።

ስልጠናውን የሰጡት ከSTEM POWER የመጡ ባለሞያዎች ሲሆኑ: ከፊዚክስ፣ ኤሌክትሪካልና ኮምፒውተር ምህንድስና፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ት/ርት ክፍሎች የተውጣጡ 25 መምህራን ስልጠናውን ወስደዋል።





በዚህም ዩኒቨርሲቲው የSTEM መምህራኖችን አቅም በመገንባት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በርካታ ተማሪዎችን እየመለመለ ስልጠና እየሰጠበት ያለውን የሳይንስ፣ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ ማእከል (STEM) ይበልጥ ለማጠናከር እንደሚረዳም ተገልጿል።

Systematic Review and Meta-analysis (SRMA) ስልጠና



በዚህ ስልጠና ከጤና ሳይንስና ሜዲካል ኮሌጅ እና ከእንስሳት ህክምና ኮሌጅ የተውጣጡ መምህራን የተሳተፉበት ሲሆን: ስልጠናውን የሰጡት በጂማ ዩኒቨርሲቲ መምህር እና ተመራማሪ የሆኑት በዘርፉ የካበተ ልምድ ያላቸው ፕ/ር ቀልኪዳን ሃሰን ናቸው::



ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የተመራማሪዎቹን የመስራት አቅም ለማሳደግ ያለመ "Systematic Review and Meta-analysis (SRMA)" ስልጠና ተሰጥቷል::

አቅም ግንባታ

የምርምር አቅም ለማጎልበት ስልጠና

የመምህራንን የምርምር አቅም ለማጎልበት ያለመ ስልጠና

የስልጠናው አላማ የመምህራንን የምርምር አቅም በማጎልበት በሜጋ የምርምር ስራዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል እና የተለያዩ የምርምር ሶፍትዌሮችን ለሜታ አናሊሲስ በመጠቀም መረጃዎችን በመተንተን ለፖሊሲ አውጭዎች ግብዓት የሚሆኑ ጥናቶችን መስራት የሚያስችል አቅም መፍጠር ነው። ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ፕብሊኬሽን ዳይሬክቶሬት ያዘጋጀው "Systematic Review and Meta-analysis (SRMA) ስልጠና ተሰጥቷል።





ለአፋር የባህልና ቅርስ ባለሙያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል::

የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና የአፋር ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር "ቅርሶቻችን ለሀገራዊ ልማትና ለማህበረሰባዊ ተጠቃሚነት" በሚል መሪ ሀሳብ ለአፋር የባህልና ቅርስ ባለሙያዎችና ባለድረሻ አካላት ያዘጋጀው ሥልጠና በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሬዶ የባህልና ሀገር በቀል ጥናቶች ማዕከል አዳራሽ ተካሂዷል።

በመድረኩ 8 ያህል ጥናታዊ በታሪክ: በአርኬዎሎጅ: በፔሊዮአንትሮፖሎጂ: በኢንታንጀብልና የኢትኖግራፊ ቅርሶች በቅርስ አስተዳደር በሙዝየም በታሪካዊ ቅርሶችና ጥንታዊ ጽሁፎች ምንነት: ፋይዳ: አጠባበቅና ተግዳሮቶች ያተኮሩ ፅሁፎች ላይ ገንቢ ምክክርና ውይይት ተደርጎባቸዋል::







አቅም ግንባታ በአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲነት ሽግግር ላይ ስልጠና

ወደ ተግባር ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ነት ሽግግር ላይ ስልጠና

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ወደ University of Applied Science የሚያደርገውን የሽግግር ሂደት የሚደግፍ እና የተግባር ሳይንስ ዩኒቨርሲቲን ተፈጥሮ እና ባህሪያት ለመረዳት የሚያስችል የአምስት ቀን የአቅም ግንባታ ስልጠና ለአካደሚክ መካከለኛ አመራር አባላት ሰጥቷል። ስልጠናው ከስትራቴጂካዊ ራዕይ አንፃር ቀዳሚ የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን ያለውን ዓላማ ለማሳካት የሚደግፍ መሆኑ ተገልጿል።ሥልጠናው በሰመራ ዩኒቨርሲቲ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በጀርመን ትብብር (GiZ) እና በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ትብብር የተተገበረ ነው።



ለተማሪዎች የተለያዩ ስልጠናዎች:

ሠመራ ዩኒቨርሲ ከAmref Health Africa የKefeta ፕሮጀክት ጋር በመተባበር 850 ለሚሆኑ ተማሪዎች የ life skills እና Effective work habits ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

ስልጠናዎቹ በተማሪዎች ሙያ ማሻሻያ ማዕከል አስተባባሪነት የተሰጡ ሲሆን:ከመደበኛ መማር ማስተማር ጎን ለጎን ተማሪዎችን ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያግዙ ናቸዉ ተብሏል::





አቅም ግንባታ

የBIM Engineering Software ስልጠና

የBuilding Information Modeling (BIM) Engineering software ስልጠና

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ኢንጅነሪንግ እና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ከ5 ትምህርት ክፍሎች ለተውጣጡ 35 ተመራቂ ተማሪዎች የ Building Information Modeling (BIM) Engineering software ስልጠና ለ15 ቀናት ተሰጥቷል።





ስልጠናው የGIZ እና construction Managment የአሰልጣኞች ስልጠና በወሰዱ መምህራን እንዲሁም በተጋባዥ አሰልጣኝ የተሰጠ ሲሆን: ሰልጠኞቹ አለም አቀፍ ሰርተፊኬት የወሰዱ ሲሆን የ Exit Exam ፈተናን ለማለፍ:ለስራ ተወዳዳሪ እና ተመራጭ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል ተብሏል::

የ 'ጋርሳ'(Garsa) ዛፍ ማገገሚያ ፕሮጀክት ስልጠና ለጭፍራ ወረዳ ማህበረሰብ



በአካባቢ ስሙ 'ጋርሳ' (Garsa) በሳይንሳዊ ስሙ (Dobera glabra) በመባል የሚታወቀውን ሀገር በቀል ዛፍ በማህበረሰብ አቀፍ መልሶ የማልማት ፕሮጀክት ላይ ያተኮረ ስልጠና ከ12 ቀበሌዎች ለተውጣጡ አፋር ክልል የጭፍራ ወረዳ ነዋሪዎች ስልጠና ተሰጥቷል።



ሀገር በቀሉ የጋርሳይቶ ዛፍ ድርቅን የሚቋቋም:እንስሳት ቅጠሉን:ሰዎች ፍሬውን ለምግብነት የሚጠቀሙት:ለመድሀኒት: ለማገዶ እንዲሁም በስሩ ለመጠለል የሚጠቅም አይነተኛ የበረሀ ዛፍ ቢሆንም፣ በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥሩ በመናመን ነው።

ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ 10 ሺ የሚሆን የጋርሳ ችግኝ በማፍላት ለህብረተሰቡ የማከፋፈል እቅድ እንደተያዘም ተገልጿል::

አቅም ግንባታ

ስለ Kobo Toolbox መተግበሪያ ስልጠና

ለመምህራን በ Kobo Toolbox መተግበሪያ ላይ ያተኮረ ስልጠና

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በኩል የተዘጋጀ በ Kobo Toolbox የሞባይል ስልክ መተግበሪያ አጠቃቀም:የመረጃ አሰባሰብ ስልት ላይ ያተኮረ የ2 ቀን ስልጠና ለመምህራን ተሰጥቷል።

Kobo Toolbox ተመራማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያወጡትን የወረቀትና የማባዣ ወጪ ለመቀነስ ፣ ጊዜ ለመቆጠብ እና ስራን ለማቅለል የሚጠቅም መተግበሪያ ሲሆን: ስልጠናው በምርምር ስራ ላይ የሚታየውን የእውቀትና የልምድ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል በተግባር የተደገፈ መሆኑ ተገልጿል።



መተግበሪያው ለአጠቃቀም ቀላልና ያለ ኢንተርኔት የሚሰራ በመሆኑ ብዛት ፣ ጥራትና ወጥነት ያለው የምርምር መረጃ ለመሰብሰብና ለማደራጀት ስለሚረዳ መምህራን በሚሰሩት የጥናትና ምርምር ውጤት ላይ የሚኖረው ፋይዳ የጎላ እንደሆነም ተጠቁሟል።

በአፋምቦ ወረዳ የማህበረሰብ አቀፍ ምርጥ ዘር ብዜት



የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ ጉድኝት ዳይሬክቶሬት በአፋምቦ ወረዳ የማህበረሰብ አቀፍ የበቆሎ ዘር ብዜት ስራዎችን በስፋት እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጿል።

ከእርሶ እደሩ የሚያጋጥመውን የምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረት መፍታት ኑሮን ለማሻሻል፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና ገቢን ከመጨመረ አኳያ አወንታዊ ውጤት የታየበት መሆኑ ተመላክቷል።



በ2016 ዓ.ም የበቆሎ ምርጥ ዘርን ተዳራሽ ለማድረግ በአላሳቦሎ እና በሁመዴይታ ቀበሌ ከ40 ሄክታር በላይ የሚሸፍን የበቆሎ መስራች ዘር ለአርሶ አደሮች ድጋፍ የተደረገ ሲሆን:ገበሬዎቹን ወደ ዘር አምራች ማህበር ለማሳደግ እየተሰራ እንደሆነም ተገልጿል።

በስልጠናው ከሁለት ቀበሌዎች የተውጣጡ 22 ከፊል አ/አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ባለሙያዎች እና የአፋንቦ ወረዳ የግብርና ባለሙያ ተሳትፈውበታል።

አቅም ግንባታ

ኢንተርንሽፕ ለሚወጡ ተማሪዎች የInduction

Internship ለሚወጡ ተማሪዎች የ Induction ስልጠና ተሰጥቷል::

Internship ለሚወጡ የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የ Induction ስልጠናውን 'ከፍታ' የተባለ ተቋም ከAmref Health Africa በሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ በ2016ዓ.ም ት/ርት ዘመን ኢንተርንሽፕ ለሚወጡ ተማሪዎች ባዘጋጀው የ"Kefeta Integrated youth development program" ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተዘጋጀ ነው::

ተማሪዎቹም ከኢንጂነሪንግ: ጤና ሳይንስ እና የእንስሳት ህክምና ኮሌጆች የተመለመሉ ሲሆን ከስልጠናው በተጨማሪ በቀጣይ የinternship ቆይታቸውን የሚያግዝ ለ4 ወራት የሚቆይ ለእያንዳንዳቸው በየወሩ የ2,000 ብር ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ተገልጿል።





"Basic Entrepreneurship Skills Training "ለመምህራን እና ለአስተዳደር ሰራተኞች ተሰጥቷል::



በሠመራ ዩኒቨርሲቲ "Basic Entrepreneurship Skills Training " ከመምህራን እና አስተዳደር ሰራተኞች ለተውጣጡ 45 ሰዎች በማኔጅመንት ትምህርት ክፍል መምህራን አማካኝነት ተሰጥቷል::

የስልጠናው አላማ ሰራተኞች ከመደበኛ ስራ ጎን ለጎን የግላቸውን ስራ በመፍጠር ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን እንድደግፉ ብሎም ለሀገር እድገት የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ለማስቻል ነው ተብሏል::



አቅም ግንባታ

"Application of GIS for Geoscience"

"Application of GIS for Geoscience" በሚል ርዕስ ስልጠና

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ "Application of GIS for Geoscience" በሚል ርዕስ ለSchool of Earth Science መምህራን ቴክኒካል ረዳቶች:የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች እንዲሁም ከ7 የክልል መ/ቤቶች የተውጣጡ 14 ባለውያዎች በአጠቃላይ ከ30 በላይ ባለውያዎች የተሳተፉበት ስልጠና ተሰጥቷል::

የስልጠናው ዋና ዓላማ የጂኦግራፊያዊ መረጃ ስርዓት (GIS) መተግበሪያን በተግባር መጠቀም:በስነ-ምድር እና በማእድን ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶችን: መረጃ የመሰብሰብ ሰራዎችን በቴክኖሎጂ ማገዝ: እንዲሁም ከኢንደስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር: አገልግሎቶች ቀላልና ዘመናዊ ለማድረግ ነው::





ለባህላዊ የጌጣጌጥ እና ማዕድን አምራቾች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ከ Shool of Earth Sciences ጋር በመተባበር በአፋር ክልል በኡዋ እና ያሎ ወረዳዎች በ sunstone እና Opal ማዕድን ላይ ተደራጅተው ለሚሰሩ ማህበራት ስልጠና ሰጥቷል ::

የስልጠናው ዋና ዓላማ ሳይንሳዊ ዘዴዎችን በመጠቀም በአካባቢው የሚገኘውን የማዕድን ሀብት በአግባቡ መጠቀም እንድችሉና ጥራት ያለው ምርት በማምረት ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆነው ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ እንድሆኑ ማስቻል መሆኑ ተገልጿል::





አቅም ግንባታ

"Training on "Scientific Writing and Publishing: Practices and Challenges"

ሳይንሳዊ አፃፃፍ እና ህትመት : ልምምዶችና ተግዳሮቶች በሚል ስልጠና ተሰጥቷል።

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ"Scientific Writing and Publishing: Practices and Challenges for Researchers and Academic Staff." በሚል ርዕስ ስልጠና ሰጥቷል:: ስልጠናው በዋናነት የትምህርት ባለሙያዎችን እና ተመራማሪዎችን በሀገር አቀፍ/አለምአቀፍ እቻ በተገመገሙ ጆርናሎች ላይ ሊታተሙ የሚችሉ ሳይንሳዊ ጽሁፎችን በማዘጋጀት ረገድ አቅምን ለማጎልበት በማለም በምርምር፣ ሕትመት፣ ሥነ ምግባርና ስርፀት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ ነው።





የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለሚሰጡ ተማሪዎች ስልጠና

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር 300 ለሚሆኑ ተማሪዎች የክረምት በጎ ፈቃድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል:: የክረምት ብሔራዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዋና አላማ ተሳታፊ ተማሪዎችን በዕውቀት፣ በአመለካከት እና በክህሎት እንዲበቁ በማድረግ ለሀገር ግንባታ፣ ብሄራዊ መግባባት፣ ለሁለንተናዊ ሰላምና ዘላቂ ልማት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው::

በዚሁ መሰረት እነዚህ ሰልጣኝ ተማሪዎች በክረምቱ ለሰመራ እና አካባቢው ማህበረሰብ ዘርፈ ብዙ በጎ ተግባራትን ሲያከናውኑም ቆይትዋል::





ጉብኝት

የUSAID ከፍተኛ አመራሮች እና የቴክኒክ ቡድን ጉብኝት

የ USAID ከፍተኛ አመራሮች እና የቴክኒክ ቡድን አባላት በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የስራ ውይይት እና ጉብኝት አድርገዋል::



አመራሮቹ ባለፈው ዓመት ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሞ በጋራ ሲሰራ በቆየው እና በ USAID የፋይናንስ ድጋፍ በሚደረግለት የከፍታ ፕሮጀክት በተሰሩ ስራዎች ላይ ለመምከር ነው::



አመራሮቹ ከአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት አብዱረህማን ከድር (ዶ/ር) ጋር በነበራቸው ውይይት ስለ ከፍታ ፕሮጀክት (USAID Integrated Youth Activity) ከዩኒቨርሲቲው የተቀጣሪነት ልማት እና ሙያ ዝግጁነት ማዕከል ጋር የተሠሩ ስራዎችን እና አጠቃላይ ስለ ዩኒቨርሲቲው ገለጻ ተደርጓል::



ጉብኝት የጅግጅጋ እና መቱ ዩኒቨርሲቲዎች ልኡክ በሠመራ ዩኒቨርሲቲ

መልካም ተሞክሮዎችን- ለጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአደረጃጀት ሪፎርም ትግበራ ዙሪያ ልምድ ለመቅሰም የመጡ ልኡካንን ተቀብሎ ልምዱን አካፍሏል። እዲሱን በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ፀድቆ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የተተገበረውን የሰራተኞች ድልድል አስመልክቶ ተግባራዊ ተሞክሮዎችን ለማካፈል ችሏል::



መልካም ተሞክሮዎችን- ለመቱ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከመቱ ዩኒቨርሲቲ የመጡ በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ሀላፊ የሚመራ የዳይሬክተሮችና የቴክኒክ ቡድን በጠቅላላ ተቋማዊ መልካም ተሞክሮዎቹን አካፍሏል። ልኡካኑ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ባለፉት አመታት እየተገበራቸው ያሉ የለውጥ ስራዎችን ከፍተኛ እና መካከለኛ የተለያዩ ስራ አስፈጻሚዎች ጋር በመሆን ተግባራዊ ተሞክሮዎችን እና የመስክ ምልከታዎችን በማድረግ ተግባራዊ ተሞክሮዎችን ለማካፈል ችሏል::



ጉብኝት

የወሎ እና ራያ ዩኒቨርሲቲዎች-በሰመራ ዩኒቨርሲቲ

መልካም ተሞክሮዎችን- ለወሎ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን

የወሎ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን የሰመራ ዩኒቨርሲቲ የHigher Education Information Management System (HEIMS) ዳታ ሶፍትዌር መረጃ አጠቃቀም እና በመውጫ ፈተና (Exit Exam) የተመዘገበውን ጥሩ አፈጻጸም ተሞክሮዎችን ለማካፈል ተችሏል።



መልካም ተሞክሮዎችን- ለራያ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከመቱ ዩኒቨርሲቲ የመጡ በፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ሀላፊ የሚመራ የዳይሬክተሮችና የቴክኒክ ቡድን በጠቅላላ ተቋማዊ መልካም ተሞክሮዎቹን አካፍሏል።



ጉብኝት

የትምህርት ሚኒስቴር ሱፐርቪዥን አባላት ምልከታ

የትምህርት ሚኒስቴር የሱፐርቪዥን አባላት ምልከታ- በሰመራ ዩኒቨርሲቲ

በትምህርት ሚኒስቴር የ2016 ዓ.ም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የድጋፍና ክትትል ስራ ለመጡ ኢንስፔክሽን ቡድን አባላት በዩኒቨርሲቲው በ2015 የስራ ዘመን የተከናወኑ ተግባራትን ገምግሞ በአፈፃፀም የታዩ ጉድለቶች አይቶ የማስተካከያ እርምት የሚወሰድባቸውን የመፍትሄ አቅጣጫ አመላክቷል።

የትምህርት ሚኒስቴር የሱፐርቪዥን አባላቱ እንደገለፁት መርሃ-ግብሩ ዩኒቨርሲቲዎችን በመቆጣጠር እና በመከታተል ውጤታማ ስራ እንድሰሩ የሚያስችል ድጋፍ ለማድረግ እንደሚጠቅም አብራርተው ከዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር ጀምሮ እስከ መምህራን እና ተማሪዎች ድረስ በየደረጃው መወያየታቸውን ተገልጽዋል::

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለሁለት ቀን ሲካሄድ የቆየው የ2016 ዓ.ም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የድጋፍና ክትትል መርሃ-ግብር በርካታ የመስክ ምልከታዎችን እና ጥልቅ ውይይቶችን በማድረግ ተጠናቋል።

የትምህርት ሚኒስቴር የሱፐርቪዥን ቡድን በምልከታው በ2015 ጥሩ አፈፃፀም ያላቸው ፕሮጀክቶች፣ ጉድለት ያለባቸው እና እየተወሰዱ ያሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማድመጥ፣ ከዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ካውንስል ጋር ሰፊ ውይይት አድርጎ መወሰድ የሚገባቸውን እርምቶች ጠቁሟል። የዩኒቨርሲቲው አመራርም የተሰጠውን ምክረ ሀሳቦች ተቀብሎ በቀጣይ ሰፊ ስራዎችን እንደሚሰራ አብራርቷል።







ጉብኝት

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ የሰው ኃብት ልማት፤ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምልከታ

የዩኒቨርስቲው ፕሬዚደንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን እና ከፍተኛ አመራሮች፤ የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፤ ተቋሙ ለቀጣይ ሊተገብራቸው ያቀዳቸውን ስራዎች ፤ ወደ አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ለመሸጋገር የተዘጋጀ ፍኖተ ካርታ እና በሌሎች መሰኮች እያደረገ ያለውን ጥረት ለቋሚ ኮሚቴው አቅርበዋል።





ቋሚ ኮሚቴው ፤ አዳዲስ የህንጻ ፕሮጀክት ማስፋፊያዎችን፣ ደረጃውን የጠበቀ ቤተ-መጻህፍት እና የህጻናት ማቆያ ፣ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ የመውጫ ፈተና ማዕከልና የፈተናዎች ባንክ ያለበት ሁኔታን እንዲሁም የመምህራን መኖሪያ ቤት የግንባታዎችን መመልከት ችሏል።

በእንስሳት ዘርፍ እና በሰርቶ ማሳያ የግብርና ጥናትና ምርምር ማእከል ፤ የባህልና ሀገር በቀል እውቀት ጥናት ማእከል ወደ ተግባራ መቀየሩ ተጠናክረው መቀጠል ያለባቸው መሆናቸውን አስገንዝቧል።



ጉብኝት

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

የሰው ኃብት ልማት፤ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምልከታ



የቋሚ ኮሚቴው አባላት ከዩኒቨርሲቲው የአመራር አባላት የተደረገላቸውን ገለፃና የመስክ ምልከታ በመነሳት በቀጣይ ተጠናክረው የሚቀጥሉና መሻሻል አለባቸው ባሏቸው ጉዳዮች ላይ የማጠቃለያ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን አበረታችና አንዳንዶቹ በተሞክሮነት የሚወሰዱ መሆናቸውን ገልጿል።

ዩኒቨርሲቲው ከክልሉ የትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር የተቋቋመው የአዳሪ ትምህርት ቤት (Afar Talent Academy)የሚበረታታ እና ብቁ እና ተወዳዳሪ የሆኑ ተማሪዎችን በመቀበል የትምህርት ዘርፉን ከታች ለመደገፍ እየተሰራ ያለውን ስራ የቋሚ ኮሚቴው አባላት አድንቀዋል።



ከተማሪዎች ጋር በተደረገ ውይይት ከመሠረተ ልማት ከማሟላት ፣ ለመማር ማስተማር ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር፣ የተግባር ትምህርት አሰጣጥ ፣ የሴት ተማሪዎች እርስ በርስ ልምድና ተሞክሮ የሚቀስሙበት ከማመቻቸት ፣ እንዲሁምተሳትፏቸውን ከመጨመር አንፃር ያሉ ጉዳዮችን መገምገሙን ቋሚ ኮሚቴው አመላክቷል።

በመጨረሻም በተነሱት ሀሳቦች ላይ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች ማብራሪያ ከሰጡ በኃላ ቋሚ ኮሚቴው በሚችለው ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ እና በዩኒቨርሲቲው በኩልም ክፍተቶችን በመሙላት ለተሻለ አፈፃፀም ጠንክሮ መስራት እንደሚገባ ተነስቷል።




ጉብኝት

ክቡር ሀጅ አወል አርባ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት

ርዕሰ መስተዳድር ክቡር ሀጅ አወል አርባ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት

የርዕሰ መስተዳድሩ ጉብኝት ዩኒቨርሲቲው ከክልል ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር ባቋቋሙት የአፋር ታለንት አካዳሚ እየተማሩ ያሉ የዓኛ ክፍል ባለ ልዩ ተሰጥኦ ታዳጊ ተማሪዎችን ለመጎብኘት ነው::



የአፋር ታለንት አካዳሚ ተማሪዎች በክልሉ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአምስቱም ዞኖች ተወዳድረው አልፈው በአካዳሚው እየተማሩ ያሉ የዓኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ:በእውቀትም በስነ-ምግባርም እየታነፁ ያሉ የቤተሰብም ሆነ የሀገር ተስፋዎች ናችው::



የክቡር ርዕሰ መስተዳድሩ ጉብኝት ተቋማቱ ለሚሰሩት ትውልድን የማነፅ ስራ ከማበረታቱም በተጨማሪ መንግስትም ሆነ ማህበረሰቡ ምንህል ለታዳጊዎቹ ትኩረት እንደሚሰጥ የሚያስገነዝብ እና ለተማሪዎቹ ደግሞ የስነ-ልቦና ከፍታን እንዲመጣ ያስችላል::



ክብረ በአላት

"ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው በህብረት እንታገል" በሚል መሪቃል የፀረ-ሙስና ቀን

ሰመር ዩኒቨርሲቲ ለ20ኛ ጊዜ በአለም አቀፍ ደረጃ የተከበረውን የፀረ-ሙስና ቀን "ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው በህብረት እንታገል" በሚል መሪ ቃልአክብሯል።

ሙስና በገንዘብ ብቻ የሚገለፅ ሳይሆን ጊዜን ፣ ጉልበትን ፣ ሀሳብን እንዲሁምሀላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት እንደ ሙስና ይገለፃል።:





በአለም እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የፀረ-ሙስና ስራዎች፣ እየተወሰዱየሚገኙ እርምጃዎችን ፣ የሀብት ምዝገባን እና ሙስናን በጋራ በመከላከሉረገድ የባለድርሻ አካላት አስተዋፅዖ የተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፅሁፍየስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ስራ-አስፈፃሚ አቶ ሁሴን ከበደ አቅርበዋል።



ክብረ በአላት

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን

18ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀን በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል::

18ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀን “ብዝኃነትና እኩልነት ለሀገራዊ አንድነታችን” በሚል መሪ ቃል በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ችግኞችን በመንከባከብ ፣ የፓናል ውይይት በማድረግ፣ የባህል ትርኢት እና የሥነ-ጽሁፍ ዝግጅቶች በማቅረብ ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጋር በደማቅ ሁኔታ አክብሯል::





የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዩኒቨርሲቲያችን መከበሩ: በተማሪዎች እና ሰራተኞች መካከል ይበልጥ ብዝሀነትን እና እኩልነትን በማሳየት መከባበርንና የላቀ ማህበራዊ ተግባቦትን ይፈጥራል::



ክብረ በአላት

የአብሮነት ቀን

"ብዝኃነትን መኖር" የአለም አቀፍ የአብሮነት ቀን ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ተከብሯል።

የአለም አቀፍ የአብሮነት ቀን ለ 26ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ14ኛ ጊዜ "ብዝኃነትን መኖር" በሚል መሪ ቃል አክብረዋል፡





የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ አባላት፣ የአፋር ክልል ቱሪዝም ቢሮ: እንድሁም በርካታ የአፋ ርብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ተቋማት የሀይማኖት አባቶች: የሀገር ሽማግሌዎች : የሰመራና አካባቢው ማህበረሰብ በጋራ በመሆን በተለያዩ ትርኢቶች በደማቁ አክብርዋል::



ክብረ በአላት

የነጭ ሪባን ቀን

ዓለም አቀፍ የነጭ ሪባን ቀን በሰመራ ዩኒቨርሲቲ አክብሯል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በሀገር ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ “መቸም የትም በምንም ኹኔታ ጾታዊ ጥቃትን ዝም አንበል” በሚል መልእክት እየተከበረ የሚገኘውን አለም አቀፍ የነጭ ሪቫን ቀን በኤች.አይቪ ኤድስ መከላከል እና መቆጣጠር፣ የሴቶች ጥቃትን በመከላከል እና የአካል ጉዳተኞች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ላይ ትኩረታቸውን ባደረጉ ዝግጅቶች አክብሯል::





በተጨማሪም የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማህበር ሰመራ ቅርንጫፍ ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ እና ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ባለሙያ ጋር በሴቶች ጥቃት ምንነት፣ መገለጫዎቹ እና የአካል ጉዳተኞች ላይ ያተኮረ ፓናል ውይይት አከናውኗል::



ክብረ በአላት

የሴቶች ቀን

ሴቶችን እናብቃ፣ ልማትና ሰላምን እናረጋግጥ!" በሚል መሪ ቃል የሴቶች ቀን ተከብሯል፡

በዓለምአቀፍ ደረጃ ለ113ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ48ኛ ጊዜ "ሴቶችን እናብቃ፣ ልማትና ሰላምን እናረጋግጥ!" በሚል መሪ ቃል የሴቶች ቀን በሠመራ ዩኒቨርሲቲ አክብሯል።



ማርች 8 ለሴቶች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ድሎች እውቅና የሚሰጥበት እና ስለጾታ እኩልነት ብሎም ስለሴቶች መብት ግንዛቤ ማስጨበጫ ቀን ሆኖ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች እና ተማሪዎች በማሳተፍ በጋራ አክብረዋል።



በፕሮግራሙ የተለያዩ የስነ ፅሁፍ ስራዎች የቀረቡ ሲሆን በትምህርት ክፍል ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ላመጡ በርካታ ሴት ተመራቂ ተማሪዎች የማበረታቻ የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል።





ክብረ በአላት

GC-Culture Day

የ2016 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች የባህል ቀን አክብረዋል::

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2016 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪወች የባህል ቀን/GC-Culture Day በደማቁ አክብረዋል::



የባህል ቀን አንዱ የሌላውን ባህል ለማድነቅ እድል ከመፍጠሩም ባለፈ ተማሪዎች የመመረቂያ ጊዜያቸው እየተቃረበ በመሆኑ በአብሮነት በግቢ ያሳለፏቸውን አመታት የሚዘክር የወደፊት የህይወት ዘመን ማስታወሻም እንደሆነ አብራርተዋል::







እውቅና እና ሽልማቶች

ሀገራቸውን በሙያቸው ላገለገሉ ሰራተኞቹ እውቅና እና ሽልማት ተሰጠ።

ሠመራ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በተለያዩ የመንግስት መሰሪያ ቤቶች ከ30 ዓመት በላይ በሙያቸው ህዝብን ላገለገሉ ሰራተኞ እውቅናና ሽልማት ሰጥቷል።





በአገልጋይነት ተምሳሌት የሆኑ የሀገር ባለውለታ ባለሙያዎችን ማመስገን ወጣት ሰራተኞችን የሚያነቃቃ እና ለአገልጋይነት ቁርጠኛ የሚያደርግ ተግባር በመሆኑ ፋይዳው የጎላ ነው።



እውቅና እና ሽልማቶች

እውቅና ለሰመራ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለሰመራ ዩኒቨርሲቲ እውቅና ሰጥቷል::

ዩኒቨርሲቲው እውቅና የተሰጠው ኮሚሽኑ በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በእጅንዳ ማሰባሰብ መድረክ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ተወካዮችን ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ሲያስመርጥ ሂደቱ በተሳካ ሁኔታ እንድጠናቀቅ ላበረከተው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነው::





ኮሚሽኑ የዩኒቨርሲቲውን አመራሮች በማመስገን ለዩኒቨርሲቲውና በሂደቱ ለተሳተፉ ከ20 በላይ መምህራን የምስጋና የምስክር ወረቀት አበርክቷል::



እውቅና እና ሽልማቶች

ፕሮፌሰር ዶናልድ ጆሀንሰን

ለ ፕ/ር ዶናልድ ጆሀንሰ በህይወት ዘመናቸው ላበረከቱት አስተዋጾ እውቅና ሰጥቷል::



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ኮሌጁን ሉሲን በማግኘት ኢትዮጵያን እና አፋርን ለአለም ባስተዋወቀው እና አጠቃላይ ስለ ሰው ዘር አመጣጥ ትልቅ አስተዋጾ ባበረከተው ታላቁ ፕሮፌሰር ዶናልድ ጆሀንሰን መሰየሙ ለተቋሙ ከፍተኛ ክብር እንደሆነ ገልፀው: በቀጣይ በጋራ ለመሰራት እንደ መነሻም እንደሚሆን አብራርተዋል።

ዩኒቨርሲቲው የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብእ ኮሌጅ ህንፃውን ሉሲ(ድንቅነሽን) ባገኙት ፓሊዎአንትሮፖሎጅስት ፕሮፌሰር ዶናልድ ጆሀንሰን ስም ሰይሞ የአሪዞና ስቴት ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች በተገኙበት አስመርቋል::በአሪዞና ስቴት ዩኒቨርሲቲ Institute of Human Origins ዳይሬክተር የሆኑት ተመራማሪ ፕሮፌሰር ዮሐንስ ኃይለሥላሴ በፕሮፌሰር ዶናልድ የተሰየመውን ኮሌጅ ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ



እውቅና እና ሽልማቶች

የምስጋና እውቅና

ዩኒቨርሲቲው ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የምስጋና እውቅና ሰጥቷል::



ዶ/ር ጉቼ ጉሌ ሱላ (የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ተ/ፕሬዝዳንት) ምስጋናውን በተቀበሉበት ወቅት የሁለቱን ዩኒቨርሲቲዎች አጋርነትና ትብብር መልካም ተሞክሮ እንደሆነ ገልፀው:በቀጣይ በሌሎች ሥራዎች አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናና እውቅና ሰጥቶታል:: በኢትዮጵያ አንደኛ ሊግ የሚጫወተው የሠመራ ዩኒቨርሲቲ እግር ኳስ ቡድን (camelboys) የእግር ኳስ ቡድኑን ከአቀባበል ጀምሮ በቆይታቸው ለሰጣቸው ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለቀና ትብብርሩና ድጋፉ ምስጋናና እውቅና ሰጥቷል::



ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች እውቅናና ሽልማት

የሠመራ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ ፕሬዚዳንት ፅ/ቤት ለተማሪዎች እውቅናና ሽልማት ሰጥቷል።

እውቅናው የተሰጠው በየወሩ ከተማሪዎች ጋር በመማር ማስተማርና አገልግሎት ዙሪያ በሚደረገው የውይይት መድረክ ላይ ነው:: እውቅናና ሽልማት የተሰጣቸው በ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ተመራቂ ለሆኑና በትምህርታቸው ጥሩ CGPA ውጤት ላስመዘገቡ እንዲሁም ለሌሎች ተማሪዎች (peer learning) ማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት ጥሩ አፈፃፀም ላሳዩ ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው::





እውቅና እና ሽልማቶች

ለሴት ተማሪዎች እውቅና

The university gave recognition to high achiever female students.



ዩኒቨርሲቲው የእውቅና ሽልማቱን የሰጠው የሴት ተማሪዎች ማህበር ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብን አስመልክቶ ግብአት ለማሰባሰብ በተዘጋጀው ዝግጅት ላይ ነው::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ሴት ተማሪዎች እውቅና ሰጥቷል። ይህም በየትምህርት ክፍላቸው ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 158 ሴት ተማሪዎች የእውቅና ሰርተፍኬት አበርክቷል።

የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን በፕሮግራሙ ላይ እንደተናገሩት እውቅናው ሴት ተማሪዎች ውጤታቸውን ጠብቀው እንዲቀጥሉ፣ ለሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና ጥሩ ዝግጅት እንዲያደርጉ እና አርአያ እንዲሆኑ እና ሌሎችንም እንዲያግዙ ያነሳሳል ብለዋል።





እውቅና እና ሽልማቶች

ለህንዳውያን ባለሙያዎች እውቅና

የሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ሲሰጡ ለቆዩ ህንዳውያን ባለሙያዎች እውቅና ተሰጥቷል::

የኢፌዲሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር : የህንድ ኤምባሲ በኢትዮጵያና የህንድ መንግስት: ከሠመራ ዩኒቨርሲቲ: ከአፋር ክልል ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በትብብር ያካሄዱት ይህ ድጋፍ ለበርካታ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሎጊያ ሆስፒታል አገልግሎቱን ሲሰጡ ለቆዩ ህንዳውያን ባለሙያዎች እና ተባባሪ አካላት የእውቅናና ሽልማት ፕሮግራም ተካሂዷል::

በእውቅና ስነ-ስርዓቱ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና አፈጉባኤ ክብርት አሲያ ከማል:የክልሉ የሴቶችና ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሀላፊ ወ/ሮ ፋጡማ መሀመድ:የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ተ/ም/ፕሬዚዳንት አደም አሊ እንዲሁም ዳይሬክተሮች ተገኝተዋል::





እውቅና እና ሽልማቶች

የተመራማሪዎች ሽልማት

ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ የምርምር ዉጤቶችን ላሳተሙ ተመራማሪዎች ሽልማት ሰጥቶአል::



ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ግንቦት 05/2014 ዓ.ም ከመምህራን ጋር ባደረጉት ውይይት የምርምር ውጤት በብዛት የሚያሳትሙ ምሁራንን ለመሸለም ቃል በገቡት መሰረት ሲሆን ፣ በዚሁ መሰረት ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ተከናውኗል ::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በታወቁ አለምአቀፍ ጆርናሎች ላይ ከፍተኛ የምርምር ዉጤቶችን ላሳተሙ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ደረጃ ለያዙት ተመራማሪዎች የSumsung A54 smart phone ሽልማትና ሰርተፊኬት ሰጥቷል::

በዚሁ መሰረት፣ ኩሴ ኡርማሌ፣በእምነት ለማ ፣ ተመስገን ገበየሁ ፣ እፀይ ወልዱ እና ከበደ ገመዳ በቅደም ተከተል ከ1-5 ደረጃን የያዙ ተመራማሪዎች ሲሆኑ ሽልማታቸውን ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን እጅ ተቀብለዋል:: በተጨማሪም ከ6ኛ-10ኛ ደረጃ ለያዙት ተመራማሪዎች ሰርተፊኬት ተሰጥተዋል::



እውቅና እና ሽልማቶች

ስቴም ማዕከል ተማሪዎች ሽልማት

የስቴም ማዕከል ተማሪዎች የሳይንስና ኢንጂነሪንግ ውድድር ላይ ተሸላሚ ሆነዋል::



የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ስቴም ማዕከል ተማሪዎች ትምህርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው በ8ኛው ሀገር አቀፍ የሳይንስና ኢንጂነሪንግ ውድድር (8th annual National Science and Engineering Fair) ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈ ሲሆን፣ተማሪዎች የሰሯቸውን የፈጠራ ስራዎች አቅርበው ተሸላሚም ሆነዋል::

ውድድሩ በሀገራችን ካሉት 30 ስቴም ማዕከላት ተማሪዎች የተሳተፉበት ሲሆን: የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ስቴም ማዕከል ተማሪ ረውዳ መሀመድ እና ጓደኞቿ በሰሩት "Flood Alert system" ፕሮጀክት አንደኛ በመውጣት አሸናፊ በመሆን የላብቶፕ እና የ10,000 ብር ተሸላሚ ሆነዋል::



የፈተና ስራዎች

የተመራቂ ተማሪዎች መውጫ ፈተና (Exit-Exam)

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ2016 እጩ ተመራቂ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና (Exit-Exam) የጤና ሳይንስ እና ህክምና ኮሌጅ 172 እንዲሁም ከግል የትምህርት ተቋማት 478 የጤና ተማሪዎችን በተሳካ ሁኔታ አስፈትኗል:: ዩኒቨርሲቲው ራሱ ያሰለጠናቸውን (1427) ተማሪዎች እንዲሁም ከተለያዩ የግል ኮሌጆችና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የተመደቡለትን ጨምሮ በድምሩ 2387 ተማሪዎችን መፈተኑን የፈተናዎች ማእከል መረጃ ያመለክታል::





ለፈተና አስፈጻሚዎች የምስጋና መርሐ ግብር ተካሄደ::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች ውስጥ ከ90% በላይ ማሳለፍ በመቻሉ ለመምህራን እና ለፈተና አስተባባሪዎች የምስጋና እና እራት ግብዣ መርሃ-ግብር አዘጋጅቷል::

በመርሐ ግብሩ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን፣ ምክትል ፕሬዝዳንቶችን ጨምሮ ሌሎች የሥራ ሀላፊዎች እና በፈተናው ማስፈፀም ላይ የተሳተፉ አካላት ተገኝተዋል::

ተማሪዎቻችን በመውጫ ፈተናው ያገኙት ውጤት በሀገር ደረጃ ከፍተኛ ሆኗል ለዚህ ስኬት ጠንክረው በማስተማርና ትውልድን በመቅረጽ አስተዋጽኦ ላደረጉ መምህራን ዩኒቨርሲቲው እንደተቋም ያለውን ክብር ለመግለጽ መርሐ ግብሩ መዘጋጀቱን የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ዶ/ር መሀመድ ኡስማን ጠቁመዋል::






ፕሬዝዳንቱ በዛሬው የእራት ግብዣ እና ምስጋና መርሐ ግብር አመቱን ሙሉ ደከመን ሳይሉ ላስተማሩ መምህራን፣ ለፈተና አስፈጻሚዎች፣ ለጸጥታ አካላት እና ማንኛውንም ተሳትፎ ላበረከቱ ሁሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል::

የፈተና ስራዎች

የማጠቃለያ ፈተና በዲጂታል መተግበሪያ (software)

ከወረቀት ነፃ የማጠቃለያ ፈተና

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2016 ትምህርት ዘመን የአንደኛ ወሰነ-ትምህርት ከ1400 በላይ የ4ኛና 5ኛ አመት መደበኛ ተመራቂ ተማሪዎችን የማጠቃለያ ፈተና በዲጂታል መተግበሪያ (software) በመጠቀም ከወረቀት ነፃ (PAPERLESS) በሆነ መልኩ ፈትኗል::





ከወረቀት ነፃ ፈተና መስጠት ጠቀሜታው የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ፣ ቀጣይነት ያለው የዘመነ የፈተና ስርዓት ለመዘርጋት እና ተበታትኖ በተለያዩ ኮሌጆች ይሰጥ የነበረውን ፈተና በአንድ ማእከል ማድረግ እና ወጪን መቀነስ አስችሏል።



የፈተና ስራዎች

የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና

ለሴት ተማሪዎች "በትምህርት ስኬታማ መሆን መቻል" ላይ ያተኮረ ስልጠና

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ለሚወስዱ ሴት ተማሪዎች በትምህርት ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እና ስኬታማ መሆን በሚቻልበት ፅንሰ ሀሳብና ልምድ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጥቷል።





ስልጠናው ሴት ተማሪዎች በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት በማስመዝገብ በወደፊት የዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የላቀ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ለማገዝ የተግባር ክህሎቶችን እንደመነሻ በመውሰድ በትምህርት ስኬታማ ለመሆን እና የህይወት ክህሎት እድገትን ለማጎልበት ያለመ ነው።



የፈተና ስራዎች

የቃል የመግባት ስነ-ስርዓት

በዩኒቨርሲቲው ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የቃል የመግባት ስነ-ስርዓት





ሠመራ ዩኒቨርሲቲ በክልሉ ከሚገኙ ሁሉም የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ 269 የ12ኛ ክፍል ተማሪወችን ለዘንድሮው የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና አስተምሮ ለማብቃት ነው::

ተማሪወች በዩኒቨርሲቲው በሚኖራቸው ቆይታ የዩኒቨርሲቲውን መመሪያዎችና ደንቦች የሚያስገነዝብ እና የመጡበትን አላማ ለማሳካት ያላቸውን ቁርጠኝነት ቃል ገብተዋል::



በስነ-ስርዓቱ ላይ የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች:የክልሉ ትምህርት ቢሮ አመራሮች :የማህበረሰብ ተወካዮች የተገኙ ሲሆን የትውልዱን ታሪካዊ አደራ የተሸከሙ ተስፋ የሚጣልባቸው ተማሪዎች በመሆናቸው የሞራል ስንቅ የሚሆን ምክር በመሰጠት ከጎናቸው በመሆን እንደሚደግፏቸው በመግለጽ አበረታተዋል::



የፈተና ስራዎች

ሞዴል ፈተና

በዩኒቨርሲቲው እየተማሩ የሚገኙት የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ሞዴል ፈተና

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ከክልል ት/ርት ቢሮ ጋር በመተባበር በክልሉ ከሚገኙ ሁሉም የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ 276 የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን አስተምሮ ለ2016 የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ለማብቃት በማለም ሚያዚያ 05/2016ዓ.ም መቀበሉ የሚታወቅ ነው::





በመሆኑም ላለፉት 70 ቀናት በዩኒቨርሲቲው መምህራን ለሀገር አቀፉ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ዝግጁ የሚያደርጉ የማጠናከሪያ ትምህርቶችን ሲወስዱ የቆዩ የ12ኛ ክፍል ተማሞቹን የመለማመጃ/model ፋተና በመስጠት ላይ ነው::

ይህ በዩኒቨርሲቲው ተዘጋጅቶ እየተሰጠ ያለው ሞዴል ፈተና የተጀመረው ሰኔ 12 ሲሆን ሰኔ 17/ 2016 እንደሚጠናቀቅ እና መደበኛው ፈተና እስከሚደርስ በቀሪዎቹ ቀናት ከመምህራን ጋር በመሆን ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በመስራት በዝግጅት እንደሚቆዩ ተገልጿል::

የ2016 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከሐምሌ 3-11/2016 ዓ.ም እንደሚሰጥ ት/ሚኒስቴር መግለፁ ይታወሳል።



የፈተና ስራዎች

መግቢያ ፈተና

የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተናዎችን ፈተነ::

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የ2016ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ለሁሉም አስፈጻሚ አካላት ኦረንቴሽን በመስጠት የተጀመረ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር 2ሺ 301 የማህበራዊ ሳይንስ እና በሁለተኛው ዙር 2ሺ 745 የተፈጥሮ ሣይንስ በአጠቃላይ ከ5ሺ በላይ ተማሪዎችን በተሳካ ሁኔታ አስፈትኗል።







የ2016ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና አስፈጻሚ አካላት ያዘጋጀው የምስጋና መርሐ-ግብር



ልዩ ልዩ ውድድሮች

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ “አንድ ሰአት ለሚሊየኖች” የጎዳና ላይ ስፖርት አካሂዷል:



“አንድ ሰአት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለሚሊየኖች” በሚል መሪ ሀሳብ የጎዳና ላይ ስፖርት እንደ ሀገር 12 ሚሊዮን እንደ አፋር ክልል 2 መቶ ሺ ሰዎች በተሳተፉበት በሰመራ ከተማ ተካሁዷል::



ልዩልዩ ውድድሮች

የጤና ስፖርት የእግር ኳስ ውድድር

የጤና ስፖርት የእግር ኳስ ጨዋታ በ8 ክለቦች መካከል ተካሂዷል::

በየአመቱ የሚካሄደውን የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት በማስመልከት በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መካከል የሰራ ዘርፎችን መሰረት ያደረጉ 8 የእግር ኳስ ቡድኖች በማቋቋም ጨዋታቸውን አድርገዋል::



የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች፣ከክልል የተጋበዙ እንግዶች እንዲሁም የግቢው ማህበረሰብ በሙሉ ውድድሮቹ ን ታድሟል::

ለዋንጫ ያለፉት Admin and Development FC ከ Geoscience FC ባደረጉት ጨዋታ Admin&Development FC 6-2 በሆነ ውጤት አሸንፎ አንደኛ ሲሆን Geoscience FC ሁለተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል:: በመጨረሻም የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች ሽልማቶችን ያበረከቱ ሲሆን የውድድሩ አሸናፊ Admin&Development FC ዋንጫ ተረክቧል::





ለ20 ቀናት ሲካሄድ የነበረው የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ያሳተፈ የጤና ስፖርት የእግር ኳስ ጨዋታ :ከጤና ጥቅሞቹ ባሻገር ማህበራዊ ትስስርን: በስራ ቦታ መነቃቃትን: በቡድን መስራትን: በስፖርት መዝናናትንና መሰል ጥቅሞችን ያስገኘ ስኬታማ የስፖርት ፌስቲቫል እንደነበር ተገልጿል::





ልዩ ልዩ ውድድሮች

የኦሎምፒክ ስፖርት ትእይንት

"ኢትዮጵያ ትወዳደር: ተወዳድራም ታሸንፍ"የኦሎምፒክ ስፖርት ትእይንት እና ችቦ ማብራት

የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ከአፋር ክልል ወጣቶችና ስፖርትና ቢሮ ጋር በመተባበር ፕሮግራሙን አዘጋጅተውታል። በክብርት አትሌት ብርሀኔ አደሬ የተመራ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ልኡካን የአፋር ክልል መንግስት ከፍተኛ አመራሮች: የሠመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት: የተለያዩ ስፖርት ትምህርት ቤቶች አሰልጣኞችና ተማሪዎች በሰመራ ስታድየም ሩጫ:ቴኳንዶ:ውሹ:ቦክስ እና ሰርከስ ትርኢቶች ቀርቧል::



የ2016 አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት "የስፖርት ቀን/የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ የ2016 አመታዊ የማህበረሰብ አገልግሎት ሳምንት "የስፖርት ቀን" በተለያዩ ስፖርታዊ ክንውኖች ተከብሯል። የስፖርት ቀን የዩኒቨርሲው ከፍተኛ አመራሮች፣ ሰራተኞች እና ተማሪዎች የተሳተፉበት የህብረት ስፖርት፣ ገመድ ጉተታ የሌሎች መሰል ጨዋታዎች በማካሄድ ፍፃሜዉን አግኝቷል



ልዩ ልዩ ውድድሮች

ፈኒ ዶጊሳ' አመታዊው የስነ-ጽሁፍ ውድድር

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ሲካሄድ የቆየው 'ፈኒ ዶጊሳ' አመታዊው የስነ-ጽሁፍ ውድድር አካሂዷል::

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ዶ/ር ሬዶ የባህልና ሀገር በቀል ጥናቶች ማዕከል የተዘጋጀ መጠሪያውን 'ፈኒ ዶጊሳ' በሚል አመታዊ የስነ ጽሁፍ ውድድር አካሂዷል ::



ይህ ውድድር ለተከታታይ በ3ዙሮች ሲካሄድ የቆየ ሲሆን በሁለቱም ቋንቋዎች በአፋር እፍ እና አማርኛ) የግጥም ስራ አቅርበው 1ኛ በመውጣት አሸናፊ ለሆኑት የ20ሽህ ብር:2ኛ ለወጡት የ10ሽህ ብር እና ሶስተኛ ለወጡት የ5ሽህ ብር ሽልማትን ከምስክር ወረቀት ጋር ለእያንዳንዳቸው ተሸልሟል።







ፈኒ ዶጊሳ' በየአመቱ የሚካሄድ ውድድር እንደሆነ እና የተመረጡ የስነ-ፀሁፍ ስራዎችን በማሳተም ወጣት ደራሲያንን ማበረታታት:ባህልን:ቋንቋን ለማሳደግ እና ጥበብን ለልማትና ለሀገር እድገት መጠቀም ማስቻል መሆኑ እሙን ነው::



ልዩ ልዩ ውድድሮች

የጂሲ ካፕ የእግር ኳስ ውድድር

በዩኒቨርሲቲው (GC Cup) የጂሲ ካፕ የእግር ኳስ ውድድር ተካሂዷል።



ምስክርነት

ስለ ዩኒቨርሲቲው የተሰጡ ምስክርነት

ሰመራ ዩኒቨርሲቲ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ በዩኒቨርሲቲው መገናኛ ዘዴዎች በወጡ መረጃዎች መሰረት የተሰጡ ገንቢ፣ አበረታች እና ሀሳቦችን ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

ከአቅም ግንባታ ሥልጠና ሥራዎች የተሰጡ ምስክርነቶች



ከእንስሳት ጤና ህክምና ሥራዎች የተሰጡ ምስክርነቶች



ከአኒሻ ሥራዎች የተሰጡ ምስክርነቶች



ከጉድኝት ሥራዎች የተሰጡ ምስክርነቶች



አርአያ ሰብእ



መሐመድ አህመዲን ሐይደራ የአፋርን የቱሪዝም ሐብት በማስተዋወቅ ገፀ ምድሩን ከነ አራዊቱ አዕዋፋቱ እና አዝዕርቱ እና ደኑን የአገር ውስጥ እና ለውጭ ሚዲያ አካላት በማስተዋወቅ በጉልህ የሚታወቁ ተንቀሳቃሽ መጽሐፍት መሆን የቻሉ የአፋር ልጅ ናቸው።

የአፋር የቋንቋ ሊቁ መሐመድ አህመዲን ሐይደራ የተወለዱት ጉቢ ኢዳሌ በተባለች መንደር በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር መስከረም 15/1945 ነው።

የቀለም ትምህርታቸውን 5ኛ ክፍል በመልካ ሰዴ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሁም 6ኛ ክፍል በማታው ትምህርት ጊዜ በወልዲያ ጢዩ ሚሽን 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 1981 ተምረው ያጠናቀቁ ቢሆንም በወቅቱ በነበረው የትምህርት ተደራሽነት አለመኖር መማር አልቻሉም።

ይህ ቢሆንም የሁለተኛ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ገብቶ የመማር አጋጣሚ ባያገኙም በእራሳቸው ጥረት በአፋር ክልል በጽ/ቤት ሥራ እያሉ የ1ኛ እና 5ኛ ክፍል የአፋርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ዝግጅት ላይ በመሳተፍ ፣ የሥነ ጥበባት የ1ኛ ፣ 2ኛ እና 5ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት በማዘጋጀት ፣ አፋርኛ ቋንቋ በቮካብረሪ/ መዝገበ ቃላት ዝግጅት በመሳተፍ ለቋንቋው የጽሁፍ እድገት ከፍ ያለ አብርክቶ አድርገዋል።

መሐመድ አህመዲን ሐይደራ

የቀድሞ ሥራ ልምዳቸው 1961 ጀምሮ እስከ 1988 በመርከበኛ፣ በሰአሊነት መጽሐፍ ዝግጅት ፣ ሰሜን ምስራቅ ግጦሽ ልማት በተለያዩ መስኮች ፤ በአፋር ክልል ምክር ቤት የቅርስ ጥበቃና ጥናት ኤክስፐርት እንዲሁም ዋና ክፍል ሃላፊ በማገልገል ባህልና ቅርስ እውቀት ባለቤት በመሆናቸው "የአፋር ማህበረሰብ ላይብረሪ" ተብሎ እሰከመጠራት አድርሷቸዋል።

ባንክ ኢንቨስትምነትና ጠቅላላ ሥራ አመራር ፣በቅርስ ሙያተኛ አቅም ግንባታ፣በልማት ሥራ አመራር ሃዳር የቅርስ ጥናት ምርምር ላይ የመስክ ሥራ በትርጉም እና የስነምድር አካባቢ ፍለጋ ጥናት ከ10 በላይ ሥልጠናዎች ወስደው ወደ ተግባር በመቀየር ለማህበረሰቡ ባህልና ወግ ማስተዋወቅና ቅርስ ጥበቃ አመሪቂ ሥራ የሰሩ የአፋር አምባሳደር በመባል ይጠራሉ።

1966 እስከ 1971 በከብት እርባታ እና ስጋ ቦርድ መ/ቤት በሰሜን ምስራቅ የማቋቋሚያ ፕሮግራም በእንግሊዘኛና አፋርኛ አስተርጓሚነት በተጨማሪ በሰርቬይንግ ረዳትነት በእንስሳት እደላ ፕሮግራም የጣቢያ ተቆጣጣሪነት በመቀጠል በመስኖ ልማት ጣቢያ ተቆጣጣሪነት፣ በህብረተሰብ አኗኗር ጥናት በረዳት ኃላፊነት በንባብ ክፍል ሰርተኛ በተደራቢ የአየር ምርመራ ጣቢ መዝጋቢነት ከአሰብ ራስ ገዝ የባህል ሰአሊነት ሲያከናውኑ ከቆዩ በኋላ 1985 የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ወደ ክልል ባህልና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ በእድገት የቅርስ ጥናት ዋና ክፍል ኃላፊ በመሆን የረጅም ጊዜ አገልግለዋል።

አርአያ ሰብእ

የቱሪዝም አባት መሐመድ አህመዲን ሐይደራ



አፋር ማህበረሰብ ባህልና ወግ በኢትዮጵያ እንዲታወቅ ያደረጉ ከአፋር ህብረተሰብ የወጡ ሁለገብ ምሁር መሆናቸውን የሚገልጽ ከካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ለ ኢትዮጵያ ቅርስ ጥናት የተፃፈ ሰነድ አስረጅ ምስክር ነው።

ሙሉ የህይወት ዘመናቸውን የአፋር ባህል ታሪክና ቅርስ በማስተዋወቅ የኖሩት መሐመድ አህመዲን ሐይደራ የባህል ሰአሊነት ልዩ ሙያ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማእከል 1986 ዓ.ም በተካሄደው ትዕይንት የአፋር ባህልና ወግ እቃዎች አስረጅ በመሆን ደከመኝ ሰለቸኝ የማይሉ ከመደበኛ የሰራ ሰዓት ውጭ ብለው ሳያንገራግሩ የሙያና ህዝብና ታሪካዊ ግዴታ አደራ በመወጣት በአፋር ህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የማይረሱ አንጋፋ ሰዎች አንዱ ናቸው።

በቋንቋ በኩል ደግሞ አፋርኛ ፣ አማርኛ፣ አረብኛ እና እንግሊዘኛ ቋንቋዎች መናገር፣ መጻፍና ማንበብ ችሎታ ጭምር የነበራቸው በመሆናቸው የአፋር ማህበረሰብ ታሪክእና ባህል በማስተዋወቅ ረገድ ከፍተኛ አበርክቶ ያደረጉ ታላቅ ሰው በመሆናቸው የቱሪዝም አባት ለመባልም ችለዋል።

መሐመድ አህመዲን ሐይደራ በሕብረተሰብ ጥናት ባካበቱት ረጅም ጊዜ ልምድ የአፋርን የቱሪዝም ሐብት በማስተዋወቅ ገፀ ምድሩን ከነ አራዊቱ አዕዋፋቱ እና አዝዕርቱ እና ደኑን ጠንቅቀውና ብጥር አድርገው ለበርካታ የአገር ውስጥ እና የውጭ ሚዲያ አካላት በማስተዋወቅ በጉልህ የሚታወቁ ተንቀሳቃሽ መጽሐፍት መሆን የቻሉ ናቸው።

መሐመድ አህመዲን ሐይደራ ጉልህ ተክለ ሰብዕናቸው የሚታወቀው ከቅርስ ጋር የተዋወቀ ዕድሜያቸውን ሙሉ በዚሁ ዘርፉ የኖሩ ተብለው ሲሆን ለዚህም በ1987 በሃገራችን በቅርስ ጥናት ላይ በእድአር ፣ የመካከለኛው አዋሽ አካባቢ በተሰሩ የአርኪኦሎጂ ግኝቶች የቅርስ ቁፋሮ ሥራዎች የመምራት ችሎታቸው ሳቢ እና ተግባቢ ጠንካራ ሥራ ወዳድ ትኩረታቸው የአፋር ማህበረሰብ ባህልና ወግ በኢትዮጵያ እንዲታወቅ ያደረጉ ከአፋር ህብረተሰብ የወጡ ሁለገብ ምሁር መሆናቸውን የሚገልጽ ከካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ ለ ኢትዮጵያ ቅርስ ጥናት የተፃፈ ሰነድ አስረጅ ምስክር ነው።

መሐመድ አህመዲን ሐይደራ ከማይረሱት የህይወታቸው ታሪክ ውስጥ ዶክተር ሞሪስ የተባሉ የሚመራ ከፈረንሳይ የቅርስ ጥናት ብድን ጋር ቁፋሮ እያደረጉ በነበሩበት ወቅት በአካባቢው በነበረው ኢሳ ማህበረሰብ በጥይት ቆስለው ለመክሰስ ወደ ኤሊዉሃ ሲመጡ በኢሀዴግ ወታደሮች እንደገና በጥይት ቢተኮሰባቸው ይህ ሁኔታ ሳይበግራቸው በጽናታቸው በመቀጠል አፋርን ለዓለም ህዝብ የሚያስተዋውቅ ቅርስ ማግኘት ችለዋል።

በሠመራ ዮኒቨርሲቲ ሬዶ የአገር በቀል ዕውቀቶች ማዕከልን አስጎብኝ እና ባለትዳርና የልጆች አባት ነበሩ።

ተቋማዊ ባህሎች

መድረኮችን በብሔራዊ መዝሙር የመክፈት ባህል

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ ማንኛውንም መድረክ በብሔራዊ መዝሙር የመክፈት ባህል ላለፉት ሶስት አመታት እየተተገበረ ይገኛል:: በዚህም የሀገር ፍቅርን:አንድነትን እና ህብረትን ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እና እንግዶች የማስታወስ ጠቀሜታ አለው::


የቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች KPI ፊርማ መከረቻ


ሀገር አቀፍ የአርበቶ አደር ት/ርት ኮንፈረንስ መከረቻ


Makerspace የኢትዮጵያና ጅቡቲ ሌቶች ስራፈጠራ አለምአቀፍ አውደ ጥናት


የአመራር ስልጠና መከረቻ


የቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች KPI ፊርማ መከረቻ


የቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች KPI ፊርማ መከረቻ

ተቋማዊ ባህሎች


የቴክኖሎጂ የምርምር ውጤቶች ማቅረቢያ አውደ ጥናት


የቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች ዐርየ ሪርማ መከረቻ


የ2016ዓ.ም የግማሽ አመት ሪፖርት ግምገማ


የከፍተኛ ት/ርት ተቋማት ሚና ለሀገር ግንባታ


1ኛው የበሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን


USAID Partnership for Lowlands Resilience Workshop

ባህልን ለእንግዶች ማስተዋወቅ

ሠመራ ዩኒቨርሲቲን ለሚጎበኙ የሀገር ውስጥ እና የውጪ እንግዶች ባህልን ከማስተዋወቅ አንፃር የዶ/ር ሬድን የባህል እና ሀገር በቀል ጥናቶች ማእከልን ከማስጎብኘት በተጨማሪ የባህል ልብስ በማልበስ ለዩኒቨርሲቲው እና ለአፋር ህዝብ እንግሳደር እንዲሆኑ እና ባህሉን እንዲያውቁት የማድረግ ስራ ተሰርቷል::



በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ የሰው ኃብት ልማት፤ ሥራ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ


ለሠመራ ዩኒቨርሲቲ ሚችጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ፡ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ እና ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የጋራ ፕሮጀክት ግምገማ


USAID Partnership for Lowlands Resilience Workshop


Makerspace የኢትዮጵያና ጅቡቲ ሌቶች ስራፈጠራ አለምአቀፍ አውደ ጥናት


የጃፓን አምባሳደር በኢትዮጵያ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት ወቅት


ፕሮፌሰር ጆናልድ ጀሀንሰን ሉሲ የተገኘችበትን 50ኛ አመት ለማክበር ሲመጡ

Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት
ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት
ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት
ታህሳስ/2017/24
www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et









Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et







Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር












Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

www.su.edu.et

ከፎቶ ማህደር











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











ገጽ- 120

Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት
ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











Samara University

የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ዜና መፅሔት

ታህሳስ/2017/24

ከፎቶ ማህደር

www.su.edu.et











ከአፋር ክልል መስህቦት አንዱ

የአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ

የአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ እ.ኤ.አ. በ1966 የተመሰረተ ሲሆን በኢትዮጵያ ሀገራችን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚታወቅ የዱር እንስሳት ጥበቃ ነው.::

በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ በዋናው ስምጥ ሸለቆ ውስጥ በ756 ኪ.ሜ ላይ የተዘረጋ ሲሆን ከአዲስ አበባ በደቡብ ምስራቅ 225 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደ ድሬዳዋና ጅቡቲ የሚወስደውን ዋና መንገድ እና የባቡር መስመር የሚያልፍበት ሜዳ ላይ ይገኛል::












በፓርኩ ውስጥ በሳቫና እፅዋት (ቁጥቋጦ፣ ግራር እና የሣር ሜዳዎች) ለተለያዩ አጥቢ እንስሳት እና የአእዋፍ ዝርያዎች መኖሪ|ያ ነው:: የጎብኝዎች መዳረሻ ነው::

አመራር

የቦርድ አመራሮች




Mr. Sileshi Girma Assefa
State Minister, Ministry of Tourism,
Chairman of Board of Samara University



Prof. Sheleme Beyene Jiru
Professor of Soil Science, Hawassa University
Vice Chairman of Board of Samara University



Dr. Hadgu H/Kiros Belay
Deputy Director General,
Manufacturing Industry Development Institute (MIDI),
Board Member of Samara University



Dr. Desalegn Mengesha Degefaw
Country Director for the Ohio
State University Global One Health Ethiopia,
Board Member of Samara University



Mr. Abdulhamid Mohammed
Deputy Director General,
Ethiopian Financial Intelligence,
Board Member of Samara University



Dr. Mohammad Usman Darasa
Asst. Prof. of International Law,
President of Samara University,
Secretary General of Board of Samara University



Mr. Abdu Musa Hussen
Mayor of Semera-Logiya City Administration,
Board Member of Samara University

ስለ እኛ

ራዕይ፡-

ዘላቂ ለሆነ አገራዊ ዕድገት ብቁ የሰለጠና የሰው ሀይል ለመፍራት ጥራት ያለው ትምህርት፤ ችግር ፈቺ ጥናትንና ምርምር፤ ዘላቂ ለውጥ የሚያመጡ የማህበረሰብና የማስፈፀም አቅም የሚገነባ ቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት መስጠት ነው።

ተልዕኮ፡-

በ2035 ዓ.ም በአርብቶ አደር ልማት ትምህርትና ምርምር በምስራቅ አፍሪካ ተምሳሌት ዩኒቨርሲቲ መሆን

መሪ ቃል፡-

ማህበረሰብን እናገለግላለን!

ዕሴቶች፡-

- ለጥራት መትጋት
- የባለቤትነት መንፈስ
- እራስን ማሻሻል
- ምክንያታዊነት
- አዳዲስ ኃሳብ ማማንጨት፤
- መቅዳትና ማስማማት
- ማህበራዊ ኃላፊነት/አገልጋይነት
- ታአማኒነት
- ተጣጣሪነት

Samara University Leadership



Mohammed Usman Daresa (PhD)
mabuazka@gmail.com











